# እምነትና አመክንዮ- የተጣመሩ ወይስ የተፋቱ?

# (Faith and Reason)

## እያመንን እናስብ፤እያሰብን እንመን

በምሕረቱ ጴ. ጉታ

Mihretu P.Guta

የመልስ ይኖረው ይሆን? መጽሐፍ ፀሐፊ

ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ፈቃድ በማንኛውም መንገድ ማባዛት
በሕግ የተከለከለ ነው።

All Rights Reserved
© ምሕረቱ ጴ. ጉታ, March 2006
Mihretu Petros Guta
E-mail: mihretup@yahoo.com

አሳታሚ
ጌጃ ቃለ ሕይወት የሥነ ጽሑፍ ክፍል
መጋቢት 1998 ዓ/ም
Published by Heywet Literature
P. o. Box 698 Tel. 011, 276 33 28/ 011,276 98 30
E-mail hiwotlit@ethionet. et
Addis Ababa, Ethiopia

በርሆቦት ማተሚያ ቤት ታተመ
መጋቢት 1998 ዓ/ም

ይህ መጽሐፍ አመክንዮንና እምነትን ትክክለኛ ቦታቸውን ሰጥተን በመያዝ " ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አሳብህ ውደድ፣" የሚለውን የጌታን ትዕዛዝ ለመፈጸም እንድንችል የሚያግዝ መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ የተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ከዕለት ተዕለት የሕይወት ጉዞአችን ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ጊዜ ሰጥተን የማናስብበት ጉዳይ ነው። ወንድም ምሕረቱ የአመክንዮና የእምነት ግንኙነት ምን ይመስላል ለሚለው ርዕስ የነበሩ አመለካከቶችን ታሪካዊ ዳራና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶቹን ዘርዘር አድርጎ እንድንገነዘብ በማድረጉ የሚያስመሰግን ስራ ሰርቷል።

ስምዖን ሙላቱ

የኢቫንጄሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ ፕሪንስፓል

በአማኙ ሕብረተሰብ አካባቢ እውቀትን የእምነት ጠላት አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ በስፋት ይታያል። ሆኖም ግን ወንድማችን ምሕረቱ በዚህች ሥራ ከታሪክ፣ ከፍልስፍናና ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጣቀስ ሁለቱ ሊነጣጠሉ የማይገባቸው የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ያሳየናል። ግሩም አቀራረብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የሥነመለኮት ተማሪዎችን በተለየ መልኩ የምትማርክ ብትሆንም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለሚያገለግሉ ሁሉ ዓይን ከፋችና ጠቀሚ እንደምትሆን በማሰብ እንዲጠቀሙባት አበረታታለሁ።

ማሙሻ ፈንታ የፔንቴኮስታል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ
ፕሪንስፓል

ፍልስፍና እንደግጥም ልብ ነዛሪ፣ ለኔ ነፍስን ሲያሳክክ የሚጣፍጥ ዓይነት ወይም ሲያምም የነፍስ ላንቃ እስኪሰነጠቅ የሚያስጮህ ይህ ነው የጥያቄና መልስ ውስብስቦሽ !...የምክንያት ጡብ ድርደራና የእምቢዩ ካብ ናዳው:: "ጥበብ" በሚል ጣፋጭና መራራ ዜማ ቅኝት ውስጥ አያሌ ጠበብት ተሟግተዋል:: ከፊሉ የነፍሳቸው ጩኸት የለስላሳውን የፍቅር ድምጽ እንዳይሰሙ ከልክሏቸው፣ በነፍስና ሥጋ ኪሳራ ወድቀዋል:: ሌሎች ደግሞ ዕውቀትንና እውነትን አስታርቀው ባንድ ልብ ድንኳን ጥለዋል:: ዛሬም ዘመናችን በፍልስፍናና በሳይኮሎጂ ፍቅር ክንፍ አውጥቷል... ታዲያ ክንፎቹ ሳይረግፉ በእውነት እንዲበሩ ለማድረግ ሁለቱን ጽንፎች ማስታረቅ ይገባል:: ምሕረቱ ጴጥሮስ ባንድ ወገን የኢማኑኤል ካንትንና የስፒኖዛን ጽንፍ ከማርቲን ሉተርና ከካልቪን ጥግ ጋር በማስተያየት "አመክንዮና እምነትን" በጣምራ ዳስሶዋቸዋል:: ወደፊት ደግሞ እያደመቀና እያሰፋ ሊያስነብበን የሚችል ድንቅ ችሎታና ብዙ አቅም እንዳለው አምናለሁ::

ደረጀ በላይነህ የቀንዲል መጽሔት

ዋና አዘጋጅና ገጣሚ

በሥነመለኮታዊ የምርምር መጻሕፍት ሜኑ ውስጥ "እምነትና አመክንዮ" ለአማርኛ አንባቢያን የተጠቀለለች እጅግ የተመጠነች ጉርሻ ናት::

የእምነትና አመክንዮ ውይይት ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት በብዙዎች የተላመጠ፣ በማንም ያልተተፋ/ያልተዋጠ ነገር ነው:: እንደዚህ ያሉ መጻሕፍት የሚወደዱትም ሆነ የሚደፈሩት እንደርሱ ባሉ ጥቂቶች ብቻ መሆኑን ወንድሜ ምሕረቱ አላጣውም:: ሆኖም ጥቂቶቹን ብዙ ለማድረግ ሌላ ዘዴ ስለሌለ ነው ይህን መጽሐፍ ሊጽፈው ግድ የሆነበት::

በቀለ ወልደ ኪዳን /የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል
ቤተክርስቲያን መጋቢ/ቀጠና ሁለት

በእንዲህ ዓይነቱ ሥራ የሚያስፈልጉን ብዙ ሰዎች ናቸው መኖራቸውን ግን የምናውቀው ብቅ ሲሉ ነው:: ምሕረቱ ብቅ ብሏል በእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይም ሁልጊዜ በአዝልቆት (Consistently) እየታየ ነው:: ለዚህ ነው አቃቤ እምነት ጥሪው እንደሆነ እንዳምን የተገደድኩት:: እባካችሁ እያመንን እናስብ ምናለበት እያሰብንስ ብናምን?

ሰሎሞን ጥላሁን

የነገረ መለኮት መምህርና ደራሲ

መሠረተ ክርስቶስ ኮሌጅ

እምነትና አመክንዮ የተሰኘውን የወንድማችን ምሕረቱ ጴጥሮስን መጽሐፍ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ። ስለ እምነትና አመክንዮ ባለን የእስካሁን አነስተኛ ግንዛቤ ያጣነውን የአመክንዮና የእምነትን ግንኙነት ልዩነትና ጠቀሜታ እንዲሁም ይህንን ባለመገንዘብ ያለንበትን ውስጣዊ ግጭትና የመረዳት ረሃብ ምላሽ የሚሰጥ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ አጭርና ምጥን ሥራ ሆኖ አግኝቼዋሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን ሚዛናዊ እውነታ በመረዳት በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ዕውቀትና መታመን ለማሳደግ ከእምነት ከፍቅርና ከትህትና የመነጨ ድፍረት እንድናጎለብት ይጠቅመናል። ወንጌልን በመስበክ፣ በማስተማርና ሌሎችን በእግዚአብሔር ቃል በማሳደግና በመምራት ላይ ላለን አገልጋዮች ጠቀሜታው ከፍተኛ ይሆናል ብዬ ስለማስብ እናንብባት እላለሁ።

ገነነ ምትኩ

የአዲስ አበባ ሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን አገልጋይና

ETC 4ኛ ዓመት ተማሪ

# አበርክቶት( Dedication)

ይህን መጽሐፍ ለፍልስፍና ትምህርት ዝንባሌን ለጫሩብኝና በዚህም ለጌታ መንግስት በጽሑፍና በማስተማር አገልግሎት የበኩሌን አስተዋጽኦ እንዳበረክት እጅግ ትልቅ ሚና በሕይወቴ ለተጫወቱት፦

ለክርስቲያን ፈላስፋ ዶ/ር ዳግላስ ግሩታዩስ (ዴንቨር ሴሚናሪ አሜሪካ)

ለክርስቲያን ፈላስፋ ተድላ ገ/የሱስ /አሜሪካ/

ለእሁድ የውይይት ግሩፕ- አዲስ አበባ

To those who have ignited in me a love for Philosophy and thus, positively impacted me to contribute to God`s kingdom through teaching and writing.

Christian philosopher Dr. Douglas Groothuis (Denver Seminary USA)

Christian Philosopher Tedela G/Yesus

(Graduate of Talbot School of Theology Biola Univ. USA)

Sunday Discussion Group-Addis Ababa

# መክፈቻ (Foreword)

በእምነትና በአመክንዮ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ በዘመን ክርስትና ከጥንት ጀምሮ ሰፊ ውይይትና ክርክር የተካሄደ ሲሆን በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በርካታ ነገረ መለኮታዊ ፣ ፍልስፍናዊና ሳይንሳዊ መጻሕፍት ተጽፈዋል:: ይህንን ጉዳይ ልብ እንድንለው እዚህ ላይ ሁለት የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል፤ እነርሱም ጠርጡሊያንና የአሌክሳንደሪያው ቀለሜንጦስ ናቸው::

ጠርጡሊያን የእምነታዊነት አራማጅ ሲሆን ተፈጥሮአዊ አመክንዮን የሚቃወምና በሞኝነት መቀበልን የሚደግፍ ሰው ነበር:: ጠርጡሊያን በአንድ ወቅት እምነትና አመክንዮ ያላቸውን ግንኙነት ሲገልጽ እንዲህ በማለት ተናግሯል፤ "ኢየሩሳሌም ከአቴንስ፣ ቤተ ክርስቲያንም ከፈላስፎች መዲና ምን አላቸው?፤ "ለዚህም ጥያቄ መልስ ሲሰጥ " ይህ ምክንያት የለሽ ሞኝነት እንደሆነ አምናለሁ፤ የማይቻል ነገር መሆኑ የተረጋገጠ ነው፤" ብሏል:: ጠርጡሊያን ለዕውቀት የእግዚአብሔር መናገር በቂ ነው፤ በመገለጥ ወደ ዕውቀት እንመጣለን ብሎ ያምናል:: ጠርጡሊያን እንዲህ ዓይነት አቋም የያዘበት ዐቢይ ምክንያት ወደ ተሳሳተ ፍልስፍና እንገባለን የሚል ሥጋት ስለነበረው ነው::

በሌላ በኩል የአሌክሳንደሪያው ቀለሜንጦስ የምጡቅ ዕውቀታዊነት አራማጅ ሲሆን የአረማውያን አስተሳሰብ ለክርስቲያን ዐቃቤ እምነት(Apologetics) አዎንታዊ ጠቀሜታ አለው ብሎ በጽኑ ያምናል::

ቀለሜንጦስ እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕግን እንደሰጠ፤ ለክርስትና እምነት ጥርጊያ መንገድ ይመቻች ዘንድ ፍልስፍናን ለግሪክ ሰጥቷል ብሎ አምኗል::

ዛሬ በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ በጥቅሉ ከአመክንዮና ከእምነት አኳያ በዕውቀት ይሁን ያለ እውቀት ሁለት አመለካከቶች ይንጸባረቃሉ፤ አንዳንዶቹ አመክንዮን የእምነት ጠላት አድርገው የሚመለከቱት ሲሆኑ ሌሎች ግን ለአመክንዮ የጎላውን ሥፍራ ይሰጣሉ:: በዚህ መሃል ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ የሚጥሩም አልጠፉም:: ይህ መጽሐፍ በእምነትና በአመክንዮ መካከል ሚዛናዊነትን እንድ ንጠብቅ ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

በኔ መረዳት እምነትና አመክንዮ ተደጋጋፊና ተሟሟይ ናቸው:: አመክንዮ ምክንያቶችን በማቅረብና በማሄስ መረጃዎችን የማጣራትና የመገምገም የአእምሮ የማሰብ ችሎታና ሂደት ነው:: እምነት ግን ከዚህ ይለያል፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እምነት እውነትን ማመንንና በእግዚአብሔር መደ ገፍን የሚያሳይ ነው::

ይሁንና በአመክንዮና በእምነት መካከል ስላለው ግንኙነትና መደጋገፍ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ነገር ያለ መሆኑ አሌ የማይባል ነገር ነው:: እምነት በአመክንዮ ላይ የተመሰረተ ባይሆንም በአመክንዮ ግን ሊደገፍ ይችላል:: ለምሳሌ በእምነት ላይ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለማምከን አመክንዮ ለዐቃቤ እምነት አገልግሎት ዐቢይ ሚና ይጫወታል::



የዚህ መጽሐፍ ዐሐፊ ከዚህ በፊት በእስልምና ዙሪያ ባሉ ወሳኝ ጥያቄዎች ላይ መልስ የያዘ መጽሐፍ የጻፈና በበርካታ መንፈሳዊ መጻሕፍትና ጋዜጦች ላይ ጠቃሚ ሂሳዊ መጣጥፎችን ጽፏል:: እንዲሁም በነገረ መለኮት ትምህርት እስከ አሁን ድረስ ባለው ተሰጥኦና ሽክም ዙሪያ በማስተማር ላይ ይገኛል:: በአብያተ ክርስቲያናት መድረኮች፣ በተለያዩ ሥልጠናዎ ችና ዐውደ ጥናቶች ላይ ጠቃሚ ትምህርቶችን ሰጥቷል፣ ጽሑፎችንም አቅርቧል:: ይህም ልምዱ ለዚህ መጽሐፍ መጻፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል::

የዚህ መጽሐፍ ፀሐፊ፣ እምነትና አመክንዮ ስላላቸው ግንኙነት ለወንጌላውያን አማኞች በተረዳው ባስተዋለው መጠን ጽፏል:: በተለይም በኛ አገር በአመክንዮና በእምነት መካከል ስላለው ግንኙነት ያለውን አመለካከት ስንመለከት የግንዛቤ ማነስና አመክንዮ የእምነት ጠላት ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ አሁን በዚህ መጽሐፍ የቀረበው ትንታኔ የተሳሳቱ አመለ ካከቶችን ለማቃናትና ሚዛናዊ ግንዛቤን ለማምጣት የማይናቅ ሚና ይጫወታል ብዬ አምናለሁ::

ይህንን መጽሐፍ በኢትዮጵያ አብያተክርስቲያናት ያሉ የቤ/ክን አገልጋዮች፣ የነገረ መለኮት መምህራንና ተማሪዎች እንዲያነቡት አበረታታለሁ:: ከፍተኛ ጠቀሜታም እንዳለው አምናለሁ::

ዮናስ አስፋው
የምስክር መጽሔት አዘጋጅና
የነገረ መለኮት መምህር

# ማውጫ (Outline)

**ርዕስ** **ገጽ**


መክፈቻ (Foreword)..................................1

መቅድም (Preface)................................. 7

መግቢያ (Introduction)............................ 10

1. የእምነትና አመክንዮ ትርጓሜ (Definition).........................14

ሀ. አመክንዮ (Reason)......................................... 17

ለ. እምነት (Faith)..............................................19

2. ታሪካዊ ዳራ (Historical Background).....................23

ሀ. አውግስጢኖስ (354-430 ዓ/ም) St Auqustine....................23

ለ. ቶማስ አኪውነስ (1224-1274 ዓ/ም) St.Thomas Aquinas......28

ሐ. ማርቲን ሉተር ( 1483-1546 ዓ/ም) Martin Luther............33

መ. ጆን ካልቪን (1509-1564 ዓ/ም) John Calvin...................39

ረ. ብሌዝ ፓስካል (1623- 1662 ዓ/ም) Blaise Pascal...............45

ሰ. የታሪካዊ ዳራ ግምገማ (Background Evaluation).............51

3. እምነትና አመክንዮ በተለያዩ ሰዎች እይታ (Different views on Faith and Reason).................................55

ሀ. መገለጥ ብቻ (Only Revelation)..................................55

ለ. አመክንዮ ብቻ (Only Reason)...................................56

ሐ. አመክንዮ በመገለጥ ላይ (Reason over Revelation)............57

መ. መገለጥ በአመክንዮ ላይ (Revelation Over Reason)......58

ረ. ግምገማ ..................................58

4. የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና (The Relationship of Faith and Reason)..................................64

5. የእምነትና አመክንዮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች (Biblical Foundation)..................................72

ሀ. እምነት (Faith).......................................................72

ለ. አመክንዮ (Reason).................................................77

6. በእምነትና በአመክንዮ ዙሪያ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች (Misconceptions)

1. አመክንዮን መጠቀም እንደ መንፈሳዊ ድካም መቁጠር........82

2. አመክንዮ በመንፈስ ቅዱስ ያለመደገፍ /ያለመታመን ውጤት ነው ብሎ ማሰብ.............................................82

3. አመክንዮ በባሕላችን ውስጥ የሚበረታታና የሚሞገስ

አይደለም ........................................87

4. ስለ እምነት ያሉን የተሳሳቱ አመለካከቶች ........................89

5. አመክንዮን እንደ ሁለንተና የማየት ችግር........................91

7. ማጠቃለያ ........................................94

የቀልፍ ሰዎች ማንነት መግለጫ..................97

- መፍትሔ ቃላት (Glossary) ........................100

የግርጌ ማስታወሻ ( End Notes) ........................104

ዋቤ መጻሕፍት (Bibliography)........................119

ንዑሳን አርእስቶች (Index )........................123



# መቅድም (Preface)

የዛሬ አንድ ዓመት ከሦስት ወር በፊት ነበር ይህን አነስ ያለ መጽሐፍ በመጣጥፍ መልክ የጻፍኩት:: በጊዜው ከሌሎች ሰዎች መጣጥፎች ጋር አንድ ላይ ታትሞ በመጽሐፍ መልክ እንዲዘጋጅ ታስቦ ነበር:: ይህም ሃሳብ የመነጨው በወንድም ተስፋዬ ሮበሌ ነበር:: ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች የታሰበው ሳይሆን ዘገየ:: እንግዲህ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ የራሴን መጣጥፍ ወደ አነስተኛ መጽሐፍ ለማሳደግ በልቤ ትልቅ ሸክም ተሰማኝ:: እነሆ መጣጥፍ ይህን መጽሐፍ ወለደ::

ስለ እምነት የሚወራውን ያህል ስለ አመክንዮ አይነገርም:: በተለይም በአገራችን ዐውድ ባብዛኛው እምነትን በሚመለከት ይጻፋል፣ ይሰበካል፣ ይዘመራል:: በአጭሩ እምነት በሃሳብ ደረጃ ግልጽ የሆነ ነገር እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ:: ይህ ማለት ግን ሁሉ ሰው ስለ እምነት ያለው ግንዛቤ በቂ ነው ማለት አይደለም:: ስለ እምነት ብዙ ይባል እንጂ በርግጠኝነት ስለ አመክንዮ የእምነትን ያህል አይወራም:: በስብከትም ሆነ በትምህርት ውስጥ አመክንዮ እንግዳ የሆነ ሐሳብ ነው::

በአንድ ጎኑ ስለ እምነት መወራቱ መልካም ሆኖ አመክንዮ ደግሞ የተሰጠው ሥፍራ ከዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ አሳዛኝ ከመሆን አልፎ በአዲሱ ትውልድ ሕይወት ውስጥ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል::

እንግዲህ በዚህ አነስ ባለ መጽሐፍ ውስጥ ሊሠራ የተሞከረው ነገር ቢኖር ይህንኑ በእምነትና በአመክንዮ መካከል የተፈጠረውን ክፍተት በተቻለ መጠን ለማጥበብ መሞከርና ሕዝበ ክርስቲያኑን በእምነትና በአመክንዮ መካከል ያለውን ዝምድና በሚገባ እንዲረዳ በተቻለ መጠን መርዳት ነው::

በዚህ ሥራ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የተሳተፉ ብዙ ሰዎች ናቸው:: ወንድሜን ተስፋዬ ሮበሌን የመጀመሪያውን ረቂቅ መላልሶ በማንበብ ጠቃሚ የሆኑ አስተያየቶችን ስለለገሰልኝ አመሰግነዋለሁ:: መስፍን ሹጌ በቃለ ሕይወት ቤ/ክ የአርባን ሚኒስትሪ (Urban Ministry) ክፍል ሃላፊ የመጀመሪያው ረቂቅ በኮምፒውተር እንዲጻፍ በገንዘብ ስለረዳኝ አመሰግናለሁ:: ሌሎችም በዚህ ሥራ ውስጥ እጃቸውን ያሳረፉትን ሁሉ፣ ረቂቁን አንብበው ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት ጊዜያቸውን የሰውትን ወገኖች በተለይም አቶ ስምዖን ሙላቱ፣ አቶ ማሙሻ ፈንታ፣ አቶ ደረጀ በላይነህ፣ አቶ ሰሎሞን ጥላሁን፣ አቶ ወርቁ ኤጀሬ፣ አቶ ዮናስ አስፋው /መፍትሔ ቃላት በማዘጋጀትና አስተያየት በመጻፍ/ አቶ ታሪኩ ደመላሽ፣ አቶ ንጉሴ ቡልቻን ተባረኩ እላቸዋለሁ::

የቀድሞ የኢቲሲ ተማሪዬን በአሁኑ ወቅት የማቴቴዎስ ጋዜጣ አዘጋጅ አቶ ሚኪያስ በላይ ንዑሳን አርዕስቶችን ስላዘጋጀልኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው:: የዚህ መጽሐፍ አሳታሚ ደረጀ አበበ /የጌጃ ቃለ ሕይወት ሥነጽሑፍ ክፍል ሃላፊ/ ረቂቁን በመፃፍ የተጉትን እህት ፀሐይ ሐይሉና ዓለምፀሐይ እውነቱን አመሰግናቸዋለሁ:: በጸሎታቸው የደገፉኝን ጓደኞቼን



በሙሉ አመሰግናቸዋለሁ:: እነዚህ ወገኖቼ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል:: እንግዲህ ከዚህ በኋላ የቀረው ሁሉ የኔ ሃላፊነት ይሆናል::

እንግዲህ ይህን መጽሐፍ በአብያተክርስቲያናት ዙሪያ ለሥልጠና በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች ውስጥ ደግሞ ለማስተማሪያነት መጠቀም እንደሚቻል ላሳስብ እወዳለሁኝ:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ሰዎች ለሥነመለኮት ትምህርት አዲስ ለሆኑ ሰዎች የሚታወቁ ስላልሆኑ አጠር ያለ ማንነታቸውን የሚገልጽ መግለጫ በመጽሐፉ በስተኋላ ተቀምጧል:: መፍትሔ ቃላት ደግሞ ከነትርጉማቸው ተዘርዝረው ተቀምጠዋል::

እንግዲህ በቅዱስ አውግስጢኖስ አባባል፣ እያሰብን እንመን እየመንን እናስብ በማለት እኔም መልካም ንባብ ይሁንልን እላለሁ::

ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን!

ምሕረቱ ጼጉታ

መጋቢት 1998 ዓ/ም

March ,2006

## መግቢያ

«ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው»ዮሐ.20፡29፣ «እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» ዕብ. 11፡1፣ዕብ. 1፣6 «ያለ እምነትም ... ደስ ማሰኘት አይቻልም»፣ «ነፋስ አታዩም፣ ደመናም አታዩም ነገር ግን ይህ ሸለቆ በውሃ ይሞላል» (2ነገ. 3፣16-17) እና ሌሎችም ከእምነት ጋር የተያያዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳቦች ለብዙ ክርስቲያኖች ትልቅ መጽናኛ ናቸው:: ሆኖም ይህ ማለት ግን ሰዎች ለእምነት የሚሰጡት ስፍራ ሁሌ ተቀባይነት አለው ማለት አይደለም:: ለምሳሌ:- በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደሚታመነው እምነት ከምክንያት ጠያቂነት ጋር የተያያዘ መሆን የለበትም:: ይህ ከሆነ፣ የእምነት እምነትነት ይጠፋና አለማመን ስፍራውን ይረከባል ብለው ስለሚያምኑ ነው:: እምነት ማለት ፈጣሪ ይህን ወይም ያን ያደርግልናል ወይም በዚህ ወይም በዚያ መንገድ ይረዳናል ብሎ ተስፋ ማድረግ ነው:: ይህ አመለካከት እውነትነት ቢኖረውም ለምን እና እንዴት በማለት ጥያቄዎችን ከሁኔታዎች ጋር በማገናኘት ማንሣት ወዳልተፈለገ አቅጣጫ



ከማምራቱ ባሻገር፣ ላላስፈላጊ ጥርጣሬና ለእምነት መክሠም መንሥኤ ይሆናል የሚል ፍርሃትም ደግሞ አላቸው:: ውጤቱም የአእምሮ ሰው ብቻ እንጂ የእምነት ሰው ከመሆን የሚያርቅ ይሆናል ይላሉ:: በዚህም ደግሞ እግዚአብሔር አይከበርም:: የሆነ ሆኖ ግን እዚህ ላይ መነሳት ከሚኖርበት ጥያቄ አንዱ እምነት ምክንያት የለሽ መሆን አለበት ወይ? የሚለው ነው:: ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው ምላሽ እምነትና አመክንዮን እንድናጣምር ወይም እንድናፋታ ሊያደርገን ይችላል:: እንግዲህ፣ ይህ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያለበት ስለሆነ በዚህ ውይይት ውስጥ ማዕከላዊ ስፍራ ይሰጠዋል::

እምነት ፈርጀ ብዙ ነው:: ለምሳሌ:- ሰው ሌላ ሰው ያምናል፣ ፈጣሪውን ያምናል፣ ራሱን ያምናል (የስሜት ሕዋሳቶቹን ያምናል) ወይም በተቃራኒ መልኩ ደግሞ ላያምን ይችላል:: ይህም አለማመን ነገሮችን ከመጠራጠር ሊመጣ የሚችል ነገር ነው:: ይሁን እንጂ እምነት ሲባል በጭፍን አንድን ነገር ማመን ነው ወይስ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል እምነት ነው ትክክለኛ አቅጣጫና ባሕርይ የሚኖረው? ማስረጃስ ለእምነት ትክክለኛነት ሁሌ አስፈላጊ ነው? ሰዎች ስለ እምነት ያላቸው ግንዛቤ እውነት የሆነውን ካልሆነው እንዲለዩ ወይም

የመለየት ዐቅም እንዲያጣ ሲያደርጋቸው ይችላል። ለምሳሌ፡- አንዲት ለበርካታ ዓመታት ባለትዳርና የልጆች እናት የሆነች ሴት ነቢያት ነን ከሚሉ ወገኖች ትዳሯን እንድታፈርስ የተነገራትን መልእክት አክብራ በመቀበል፣ የሞቀ ትዳሯን እንዳፈረሰች ሰምቼአለሁ። በሌላ መልኩ ደግሞ አማኝ የነበረ ሰው፣ ወደ ውጭ አገር ሄዶ እስከ ፒ.ኤች.ዲ. ድረስ ከተማረ በኋላ እምነት እንደማያስፈልግ በማሰብ ክርስትናውን ትቶ ኢ-አማኒ የሆነ ሰው ዐውቃለሁ።

እንግዲህ ብዙ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር ግን ማመን ማለት አእምሮን መጣል ማለት ነው? በአእምሮ ከማሰብ ዓለም ጡረታ መውጣት ማለት ነው? እንዴትና ለምን በማለት የመልእ ክቶቹን ተአማኒነት እንኳ ለማረጋገጥ እንደሚቻል ዘንግተን፣ እግዚአብሔር የሰጠንን የማሰብ ስጦታችንን ተብትበን አስረን በደመ ነፍስ መንቀሳቀስ የእምነት ዋነኛ ባሕርይ እንደ ሆነ ማሰብ እየተለመደ ነው። ለዚህም ሰበቡ «እምነታዊ እምነቱን የሚመሠርተው በእምነት ላይ ነው። በመሆኑም እንዲህ ዐይነት ሰው ለማመን ምክንያቶች የሉትም።»[1] ስለ እምነታዊነት (Fidiesm) የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 ይመልከቱ። የእምነት መሠረት ከምክንያቶች «የጸዳ» ከሆነ፣ እስከምን ድረስ ነው? የእምነትና የአመክንዮ ኳስ መንከባለል ያለበት በአንድ ሜዳ ላይ ነው ወይስ በሁለት የተለያዩ ሜዳዎች? በአንድ ሜዳ ከሆነ ደግሞ፣



የአጫዋወታቸው ይዘት ምን ይመስላል?

እነዚህና እነዚህን መሰል ጉዳዮች ይህ ጽሑፍ ትኩረቱን ሰጥቶ ከሚታገላቸው ጥያቄዎች ውስጥ የሚካተቱ ይሆናሉ። የዚህ ጽሑፍ ዋና ዐላማ በእምነትና በአመክንዮ መካከል ያለውን ዝምድና መቃኘት ይሆናል። ይህንም ለማድረግ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ይከተላል፡-

በምዕራፍ 1. የእምነትና የአመክንዮ ትርጓሜ ይተነተናል፣

በምዕራፍ 2. በእምነትና በአመክንዮ ላይ የታሪካዊ ዳራ ቅኝት ይደረጋል፣

በምዕራፍ 3. እምነትና አመክንዮ በተለያዩ ሰዎች እይታ ምን እንደሚመስል ቅኝት ይደረጋል፣

በምዕራፍ 4. የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና ይታያል፣

በምዕራፍ 5. የእምነትና የአመክንዮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይተነተናል፣

በምዕራፍ 6. በእምነትና በአመክንዮ ዙሪያ የሚነሡ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ይቀርባሉ፣

በምዕራፍ 7. ማጠቃለያ ይሆናል።

# ምዕራፍ አንድ
## እምነትና አመክንዮ

እምነትና አመክንዮ እምብዛም ለመረዳት የማይከብዱ የሚመስሉ፣ ሆኖም ግን ለብዙ ዘመናት የነገረ-መለኮታውያንንና ፈላስፎችን እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ዘንባሌው ያላቸውን ሳይንቲስቶች ሳይቀር ያወዛገቡ ነገሮች ናቸው::በዚህ ዙሪያ እየተደረገ ያለ ውይይትም እስከ ዛሬ ቀጥሏል:: እኔም በዚህ ስፍራ ወደ ጽሑፉ ዋና ሃሳብ መግባት የምፈልገው የእምነትንና የአመክንዮን ትርጓሜ በማስቀመጥ ይሆናል::

«አመክንዮ (reason) ማለት ምክንያት ሰጠ፣ ምክንያት አቀረበ ከሚለው የግእዝ ቃል የመጣ ነው::»[2] አንድ የፍልስፍና መዝገበ ቃላት ደግሞ «አመክንዮ ሰዎች እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ኃይል ላይ እንዲደርሱ የሚያበቃቸው ነው::»[3] በማለት ይፈታዋል:: በሌላ የፍልስፍና መጽሐፍ ውስጥ እንደተቀመጠው ደግሞ «አመክንዮ የሰው አእምሮ እውነትን ፈልጎ የሚያገኝበት የተፈጥሮ ችሎታ ነው::»[4] ለታላቁ የነገረ መለኮት ሊቅና ፈላስፋ አውግስጢኖስ «አመክንዮ በሌሎች ነገሮች መካከል



ሰዎች ያላቸው የሚያስቡበት ማዕከል (faculty) ነው:: በዚህም ቁሳዊ ያልሆኑ እውነታዎችን ዓለም ማየትና ማወቅ የሚችሉበት ነው:: ይህም እግዚአብሔርን ጭምር ያጠቃልላል::»[5]

ከላይ የተቀመጡ ትርጓሜዎች ስለ አመክንዮ ምንነት መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤ ሊያስጨብጡን የሚችሉ ናቸው:: የራሴን ማጠቃለያ ከመስጠቴ በፊት ግን የእምነትን ትርጓሜ ማየታችን ደግሞ የበለጠውን እምነትንና አመክንዮን በሚመለከት የምናደርገውን ውይይት በተቃና መልኩ እንድንከታተል ያስችለናል:: እምነት በብዙ ዐይነት መንገድ ሊፈታ ይችላል:: ለዚህ መንሥኤው የየሰው የሃይማኖት፣ የንጽሮተ ዓለም (World View)ና የባሕል ዳራ አንድ ዐይነት ባለመሆኑ ነው::

በ1993 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት እምነትን፣ «ሃይማኖት፣አምልኮ፣ እርግጠኝነት፣ ኃላፊነትና ታማኝነት»[6] በማለት አስቀምጦታል:: በስተ ፊን ኢቫንስ በተዘጋጀ የፍልስፍና መዝገበ ቃላት ውስጥ ደግሞ፣ «እምነት በክርስትና ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ የአለኝታ ፍላጎት ነው:: ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ የሆነ ኅብረት ለመመሥረት የሚያስችሉትን ስለ እግዚአብሔር

የሚታመኑ ነገሮችንና ደግነቱን ያጠቃልላል:: በርካታ የነገረ መለኮት ምሁራን እምነት ፈርጀ ብዙ እንደ ሆነ ይገምታሉ:: ይህ ደግሞ አለኝታ ማድረግ (Trust) በቃላት የተገለጹ እምነቶችንና በታዛዥነት ለመኖር ፈቃደኛ መሆንን ያጠቃልላል:: እስከ አሁን ካየነው ለቀቅ ባለ መልኩ ደግሞ «እምነት» የሚል ቃል ለተ ለያዩ የሃይማኖት ክፍሎችና ዓለማዊ ለሆኑ (Secular) የእምነት ጉራዎችም ጭምር በጥቅም ላይ የሚውል ነው. . . ቃሉ በዋና ዋና የዓለም እምነቶች ውስጥ ሃይማኖት ከሚል ቃል ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል::»[7] "የሃይማኖት ፍልስፍና" በሚል መጽሐፉ ውስጥ ኢቫንስ አክሎ የእምነትን ተፈጥሮ በግልጽ አስቀምጦታል:: «እምነት (Faith) የሚል ቃል የሚያሳየው አንድ አማኝ መረጃ አድርጎ በመደገፍም ሆነ በተቃራኒ መልኩ ወደ ሃይማኖታዊ እውነት የሚያመጣቸውን ግምቶች፣ አቋሞችና ፍላጎቶች ወይም ዝንባሌዎችን ነው::»[8] «እምነት መሰጠትን ያካትታል»[9] «እምነት ኅሊናዊ (Subjective) የሆነውን የሰዎች ምርጫ ያመለክታል:: ይህም ክርስቲያን በመሆን ውስጥ ሊገለጽ የሚችለውን ወጥ የሆነ የመሰጠትን ዐይነት ለማመልከት ነው::»[10]

ወደ ሚቀጥለው ትንታኔ ለመሄድ እስከ አሁን የተመለከትናቸውን የአመክንዮና የእምነት ትርጓሜ



ዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው::

## ሀ. አመክንዮ (Reason)

አመክንዮ ከማሰብ ጋር የተቈራኘ ነው:: ስለ ሆነም አመክንዮ አንድን አሳብ መመርመር፣ ድምዳሜ መፈለግ፣ ማውጣት ወይም ማውረድ በሚል መልኩ ሊታይ ይችላል:: አሁን እዚህ ከያዝነው ጭብጥ አኳያ ግን አመክንዮ መገናኘት ያለበት መመርመር ወይም ድምዳሜ መፈለግ ከሚለው አሳብ ጋር ይሆናል::

«ሰው በሕይወት እስካለ ድረስ አለማሰብ ምን እንደሚመስል ማሰብ ሊቸግረው ይችላል:: ላለማሰብ ጥረት ቢያደርግም ላለማሰብ እንኳ ማሰብ ስለሚኖርበት አለማሰብ እንደሚቻል መገመት የማይቻል ባይሆንም የሚከብድ አካሄድ ይሆናል:: ሰው በተፈጥሮው የሚያስብ ፍጡር ነው:: ሆኖም ስለ አንድ ነገር በጭፍን ነገሮችን ሳያገናዝብ አቅጣጫ የለሽ ማሰብ የሚያስብ ከሆነ ባወጣኝ ቦታ እወጣለሁ ብሎ የሚያስብ በመሆኑ፣ አስተሳሰቡ ራሱ ግልጽ ላይሆን ይችላል:: ይህም ከአመክንዮ መራቅን ሊያሳይ የሚችል አካሄድ ነው:: አስተሳሰባችን አመክንዮአዊ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ ተለይቶ የሚታወቀው

አስተሳሰባችን ከሎጂክ ወይም አቅጣጫ ከሚያስይዙ የአስተሳሰብ መርሖች ጋር ሲስማማ ነው::»[11] ሥነ-አመክንዮ በሥርዐት የማሰብ ጥበብ ሲሆን የራሱ የሆኑ መርሖች ደግሞ አሉት ለምሳሌ ሦስቱን ብቻ እንመልከት

ሀ. የተቃርኖ ሕግ (The Law of non-Contradiction) አንድ ነገር በአንድ ጊዜ አንድም ሌላም ነገር ሲሆን አይችልም::

ለምሳሌ:-«ሀ»፣ «ሀ» እና «ለ» በአንድ ጊዜና መንገድ «ሀ»ም «ለ»ም ሊሆን አይችልም

ለ. ዘ ሎው ኦፍ ኤክስክሉድድ ምድል (The Law of excluded middle) አንድ ነገር ይህ ወይም ያ ነው::

ለምሳሌ:-መኪና፣ መኪና ወይም አይደለም::

ሐ. ዘ ሎዉ ኦፍ አይደንቲቲ:- (The Law of identity) አንድ ነገር ያ ነገር ብቻ ነው ለምሳሌ:-ጠረጴዛ፣ ጠረጴዛ ብቻ ነው::

በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ በግርጌ ማስታወሻ ሥር ተጨማሪ ማብራሪያ ይገኛል::[12] እንግዲህ አመክንዮ የሰውን አእምሮ በማሰብ ሥራ ላይ እንዲሠማራ የሚያደርግ የሥነ-አመክንዮ (Logic) ማዕከላዊ አካል ነው:: በመሆኑም "አመክንዮ ማለት ስለ አንድ ነገር ምንነት የሚታመነውንና የሚባለውን ነገር



እውነትነትና ውሸትነት ለማወቅ በግምገማዊና በትንተናዊ መንገድ የአመክንዮ መርሖችን በመከተልና በመጠበቅ፣ በአንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚደረግ ጉዞ ነው::"[13] እነኚህን መሠረታዊ የሆኑ የሥነ አመክንዮ መርሖችን መመልከት የጽሑፌ ዓላማ ባለመሆኑ ለማወቅ ለሚፈልጉ አንባቢያን በጋይዝለር የተጻፈውን «መግቢያ ለሥነ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ» (Introduction to Logical Thinking (1990) ወይም (Patrick J.Hurley A concise Introduction To Logic. 5th edition 1994) የሚሉ መጻሕፍት እንዲያነቡ እጋብዛለሁ::

## ለ. እምነት (Faith)

ከብዙ ክርስቲያን ወገኖቼ ጋር ባለኝ ግንኙነት ዘወትር ከማስተውላቸው ነገሮች ውስጥ ሰፊ ሥፍራ የያዘው በእምነት ዙሪያ ያለ ግንዛቤ ነው:: ይህን ምልከታዬን በጥሩ ዐይነት መልኩ አሜሪካዊው ፈላስፋ ጄ.ፒ ሞርላንድ የሚባል ሰው ገልጾታል:- «ለብዙዎች ሃይማኖት ከኀሊናዊ ስሜት ጋር፣ ከበጎ ተነሣሽነት፣ ከግላዊ ሃይማኖተኛነት/ ቅድስና እና ጭፍን እምነት ጋር የተያያዘ ነው::»[14] ሃይማኖታዊ እምነት በመሠረቱ ባዶ ወይም ይዘት የሌለው ተደርጎ ሲታሰብ የ 17ኛ ክፍለ ዘመን ታላቁ ሳይንቲስትና ዐቃቤ እምነት (apologist) ብሌዝ

ፓስካል እንደ ተናገረው፣ ወደ ሁለት ጽንፎች ያስሄዳል:- «አመክንዮን ማስወገድ፤ አልያም አመክንዮን ብቻ ማመን»[15] ይሁን እንጂ እምነት ከማሰብ ጋር ቁርኝት የሌለው ተደርጎ መወሰዱ ትክክለኛ አካሄድ ላይሆን ይችላል:: እምነት የአማኙን (የባለቤቱን) ፈቃድ የሚያካትት በመሆኑ አንድ ነገር ከማመዛዘንና አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከሚደረግ ሂደት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው ነገር ነው:: በግሌ በእምነት የሚወሰደው ነገር ሁሌም በተሟላ መረጃና ግልጽ በሆኑ ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ ነው የሚል በአራት ነጥብ የተቋጨ አመለካከት የለኝም:: ከዚህም በመነሣት፣ «አንድ ነገር በምናምንበት ጊዜ ይብዛም ይነስ፣ ብናስተውለውም ባናስተውለውም ምክንያት ሊኖረን እንደሚችል እገምታለሁ:: ያለ ምንም ምክንያት አንድን ነገር ማመን በራሱ በመሠረት የለሽ ምክንያት እንደ ማመን ሊቆጠር ይችላልና:: ይህ አመለካከቴ ግን በሁሉ ሰው ዘንድ ተቀባይነት ባይኖረውም እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው የማሰብና የማመዛዘን ችሎታ ስለሰጠው ነገሮችን በጭፍን ማድረግ፣ ማመንና መወሰን ያለምንም የማሰብ ችሎታ ከሌለው በደመ-ነፍስ በልቶና ጠጥቶ ከሚኖር እንስሳ እንደማይለየው»[16] እንዲታሰብ በር ሊከፍት ይችላል:: እንግዲህ የእምነት ትርጓሜ እንዴት ይቋጭ? ለሚለው ጥያቄ አር.ሲ.



ስፕሮል የሚባል ዕውቅ የነገረ መለኮት አስተማሪ ከወዳጆቹ ጋር በጻፈው «ክላሲካል አፖሎጀቲክስ» በሚል መጽሐፉ ውስጥ ስለ ትክክለኛው እምነት ምንነት ያነሳቸውን ሦስት ነጥቦች በራሴ መንገድ ላብራራ:- እምነት ሦስት ገጽታዎች አሉት:-

1. **የዕውቀት ገጽታ:-** (Knowledge dimension) ይህ ማለት የምናምነው ነገር የሚታወቅ መሆን አለበት:: ነገሩ አሁን በአሁን ለእኛ ግልጽ ላይሆን ይችላል:: ባብዛኛው የሚረዳን ከመሬት ተነሥተን «ይህን ወይም ያን» አምናለሁ ማለት ሳይሆን፣ ስለምናምነው ነገር በቅድሚያ የጨበጥነው ግንዛቤ መኖሩ ነው፣ እምነትን ይዘት እንዲኖረው የሚያደርገው:: ለምሳሌ ወንጌል ይዘት አለው:: ይህም ይዘት፣ ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ሰው፣ ስለ ድነትና ፍርድ የመሳሰሉ ነገሮች ያስተምረናል:: በወንጌል የሚያምን ሰው ስለ ወንጌል ምንነት የማወቅ ግዴታ ይኖርበታል::

2. **የልብ ገጽታ:-** (Heart dimension) አእምሮአችን ከልባችን ጋር መስማማት አለበት:: ማመን የምንችለው ስለ አንድ ነገር ዕውቀት ስላለን ብቻ ሳይሆን፣ ልባችን ነገሩን ሲተገብረውና ከአእምሮአችን ጋር ሲስማማ ነው::ይህ የልብ

ገጽታ የተባለው የሚያተኩረው አእምሮአዊ ዕውቀትን ወደ ተግባራዊ ዕውቀት በመመንዘር ላይ ነው::

3. **የማመን ውሳኔ ገጽታ:-** (Trust dimension) አእምሮአችን ከልባችን ጋር በተስማማበት ነገር የእኛ ለማመን የምንወስደው ውሳኔ እጅጉን ጠቃሚ ነው:: የግል ውሳኔ ሲኖረን ነው ይህ የሚሆነው:: «እምነት» ደግሞ ምሉዕ የሚሆነው ወደ ክርስቶስ የሚያስጠጋንም በግል ለማመን የምናደርገው ውሳኔ ነው»[17]፤ ስለዚህ ከዚህ የምንረዳው እምነት በራሱ ሽፍን ነገር ሳይሆን፣ የራሱ የሆነ አቅጣጫ፣ ይዘትና ምክንያት ያለው ነገር መሆኑን ነው::



# ምዕራፍ ሁለት

## <u>ታሪካዊ ዳራ</u>

እምነትና አመክንዮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ቁልፍ ስፍራ አላቸው:: በተለያዩ ዘመናት ፈላስፎችና ነገረ መለኮታውያን በየራሳቸው መንገድ የእምነትና የአመክንዮን ምንነት ሊረዱ ሞክረዋል:: ለቀጣዩ ግንዛቤያችን ይረዳን ዘንድ እስቲ በዚሁ ዙሪያ ተነሥተው የነበሩትን ውይይቶች በአጭሩ እንቃኝ::

### <u>1. አውግስጢኖስ (Augustine) (354-430 ዓ.ም)</u>

በሰሜን አፍሪካ በሂፖ ቄስ የነበረው አውግስጢኖስ ከአዲስ ኪዳን ሐዋርያት በኋላ ከተነሡት ታላላቅ የቤተክርስቲያን አባቶች አንዱ ነው:: ከዚህ ባሻገር አውግስጢኖስ እውቅ ፈላስፋና የነገረ መለኮት ሊቅ ነበር::

አውግስጢኖስ በጣም ከሚታወቁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ ከመሆኑ ባሻገር ለክርስቲያናዊ እምነት በርካታ ነገሮችን ያበረከተ ታላቅ ሰው ነው:: በተለይም ደግሞ «የመጽሐፍ

ቅዱሳዊ እምነት ፅንስ ሐሳብ (concept) ግልጽ በሆነ መንገድ ከግሪክ ዕውቀትና እምነት ጋር ያቆራኘ ታላቅ ሰው ነው።»[18] አውግስጢኖስ አመክንዮን ባይቃወምም ለሥልጣን /ለበላይ አካል/ የሚሰጠው ግምት ከፍ ያለ ነው። የዚህ ሥልጣን ምንነት የሚደገፈው በቅዱሳት መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን ላይ ነው። አውግስጢኖስ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንነት መሠረት ሆነው የሚያገለግሉ ሁለት ነገሮች ትንቢትና ተአምራት ናቸው ብሎ ያምናል። አውግስጢኖስ የአመክንዮ ከሥልጣን ጋር ያለው ትስስር «ሥልጣን እና አመክንዮ በመተባበር ሰውን ወደ እምነት ማምጣታቸው ነው።"[19] ብሎ ያምናል። አውግስጢኖስ እምነትን የሚፈታው «እምነት የማይታይ ነገርን መቀበል ወይም ከማይታይ ነገር ጋር መስማማት"[20] እንደ ሆነ ነው። ለአውግስጢኖስ በእምነትና በአመክንዮ ላይ ላለው አመለካከት በመሠረትነት የረዳው በግሪኩ የብሉይ ኪዳን ቅጅ (ሰባዐ ሊቃናት ትርጉም) Subtuagiant ኢሳይያስ 7:9 ላይ የሚገኘው አሳብ ነው። ይህም «ካላመንህ በስተቀር አትገነዘብም»[21] የሚል ሐረግ ነው። ብዙዎች ይህንን ሐረግ በማንበብ አውግስጢኖስ በአመክንዮ እንደማያምንና ይልቁንም



ለእምነት ብቻ ስፍራ የሚሰጥ እምነታዊ (Fideist) እንደሆነ ይቆጥሩታል። ሆኖም አውግስጢኖስ ራሱ የተናገራቸውን ነገሮች በማየት ለመረዳት እንደምን ችለው ማመን ከማሰብ ተነጥሎ አይታይም። በእርግጥ ዕውቁ ክርስቲያን ፈላስፋ ዊሊያም ክሬግ እንዳስተ ዋለው «አውግስጢኖስ በእምነት ላይ ያለውን ዝንባሌ ለመተርጐም በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም አመለካከቶቹ በዓመታት ውስጥ ያደጉና የሰፉ በመሆናቸው ነው»።[22] ለምሳሌ አውግስጢኖስ፤ እምነትና አመክንዮን በተለየ መልኩ የሚያይበት መንገድ እንደ ሆነ ተደርጎ ሊታይ እንደሚችል በአንዳንዶች ዘንድ ይታመናል። አመክንዮ አርስጣጣሊሳዊ ( Aristotleian) ሥነ አመክንዮ በመሆኑ ፈንታ እንደ አውግስጢኖስ መረዳት አመክንዮ በሥነ ልቡናዊ አካሄድ የአእምሮ «ዕይታ» (Vision) ነው። የዚህ «ማየት» (Seeing) መጨረሻው ዕይታ ነው። ይህም አንድን የታወቀ እውነታ በግልጽ ማየት መቻል ነው።»[23] በሌላ አገላለጽ ለአውግስጢኖስ፣ በእውቀትና በማመን (Belief) መካከል ልዩነት አለ። እውቀት (Knowledge) ማለት ለአውግስጢኖስ አንድን ነገር በምንጩታዊ ወይንም (Deductive) መንገድ በሚደረስ ድምዳሜ ላይ በመደገፍ የሚጨበጥ ነገር ሳይሆን፣

በቀጥታ አንድን ነገር ማወቅ ነው። ማመን ግን ሰዎች ወይም የመረጃ ምንጮች በሚሰጡን መሠረት ላይ በመቆም የምንወስደው ወይም ስለ አንድ ነገር ምንነት የምናገኘው ግንዛቤ ነው። የአውግስጢኖስ እውቀትንና ማመንን በምን ዓይነት መንገድ እንደተረዳቸው ለማወቅ መረዳት ያለብን ነገር አለ። ይኸውም እውቀት ለአውግስጢኖስ ያለማንም ዕገዛ ሊታወቅ ያለን ነገር ማወቅ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን መኖር ለማረጋገጥ የሌላ ሰው ምስክርነት አያስፈልገው ይሆናል። የራሱን በዚህ ምድር መኖር፣ በሕይወት እስካለ ድረስ በቀጥታ ያውቀዋል። በርግጥ ይህን ምሳሌ የሚቃወሙ ሰዎች ቢኖሩም የራስ መኖር በትምሕርት የሚረጋገጥ ሳይሆን በቀጥታ የሚታወቅ ሐቅ ነው። የአስራ ሰባተኛው ዘመን ፈረንሳዊው ፈላስፋ የዲካርት ምሳሌ ጠቃሚ ነው። " I think; therefore I am" ስለማስብ ስለዚህ አለሁ። አንድ ሰው መኖሩን የሚጠራጠር ከሆነ፣ ለዚያው ለጥርጣሬውም እንኳ መኖር መቻሉ የግድ ይሏል። በመሆኑም የራሱን መኖር የሚጠራጠር ሰው ቢያንስ ለመጠራጠር መኖር ስለሚኖርበት የራስን መኖር ለማወቅ ከራሳችን ውጭ በቀዳሚነት አሳማኝ የሆነ መረጃ አይኖርም በማለት መቋጨት የሚቻል



ይመስለኛል። ማመን ግን ለአውግስጢኖስ ከእውቀት ለየት ባለ መልኩ በተለያዩ መረጃዎች ላይ በመደገፍ የሚወሰድ የግንዛቤ ርምጃ ነው። ለምሳሌ፡- አየለ የበቀለ ልጅ መሆኑን በቀጥታ አናውቅም። በተለያዩ መረጃዎች ላይ በመደገፍ አየለ የበቀለ ልጅ መሆኑን ግን እናምናለን። ይህም የአየለን የልደት ሰርተፊኬት በማየት፣ አብሮ በማደግ፣ አየለ ቡአቶ በቀለ ቤት መኖሩን በማየትና አቶ በቀለ ለአየለ የሚያደርጉለትን እንክብካቤ በማየት፣ ሌሎች ሰዎች አየለ የአቶ በቀለ ልጅ መሆኑን በሚሰጡን ምስክርነትና... ወዘተ ማረጋገጥ እንችላለን። ከዚህ ባሻገር አውግስጢኖስ ማሰብን ያላካተተ ማመን ሊኖር እንደማይችል ሲናገር፣ «ማንም ቢሆን ሊታመን ስላለው ስለዚያ ነገር በቅድሚያ ሳያስብ ምንም ነገር አያምንም»[24] ብሎአል። በመቀጠል አውግስጢኖስ የማመንና የማሰብን ትስስር ጠበቅ አድርጎ ያስቀምጠዋል። «የሚያስብ ሰው ሁሉ የሚያምን አይደለም፤ ሰበቡም ብዙ ሰዎች ላለማመን ሊያስቡ ስለሚችሉ ነው፤ ነገር ግን የሚያምን ሁሉ ያስባል። በማመን ያስባል በማሰብ ያምናል።»[25] አውግስጢኖስ በአመክንዮ ላይ ያለው ጠንካራ አቋም ግልጽ የሆነበት ዐረፍተ ነገር እንዲህ ይነበባል፣

«እግዚአብሔር ራሱ ከሌሎች ፍጥረታት አስበልጦ የሠራልንን በእኛ ውስጥ ያለውን ያን የአመክንዮን ክፍል መጥላትን ይከለክላል:: ስለዚህ ለምናምንበት ነገር ምክንያት ሳንቀበል ወይም ሳንፈልግ ለማመን አማኞች መሆን ይገባናል:: አመክንዮአዊ ነፍስ ባይኖረን ኖሮ ፈጽሞ ማመን አይቻለንም::»[26] የሰውን የሕይወት መርሕ በተመለከተ «እግዚአብሔር በአመክንዮአዊ መንገድ የማመዛዘንና የማሰብን ችሎታ በሰው ውስጥ አኑሮአል::»[27]

እስከአሁን በጥቂቱ ካነበብነውና ከተደረገው አጠር ካለ ውይይት በመነሣት መረዳት እንደምንችለው ከሆነ፣ አውግስጢኖስ አመክንዮንና እምነትን የሚያየው አፋትቶ ሳይሆን ኖርማን ጋይዝለር እንደ ደመደመው «ለአውግስጢኖስ የአመክንዮ እገዛው ሰው በወንጌል እንዲያምን፤ ከማመኑ በፊት፣ ሲያምንና ካመነም በኋላ በጥቅም ላይ መዋሉ ነበር::»[28]

## ቶማስ አኪውነስ Thomas Aquinas (1224-74 ዓ.ም)

በ13ኛው ክፍለ ዘመን ተነስተው ከነበሩ ስመጥር ፈላስፎችና ነገረመለኮታዊያን መካከል አንዱ ነው:: የአሪስጣጣሊስን የስነ አመክንዮ ሕጎች



ከክርስትና እምነት ጋር በማገናኘት ትልቅ ሚና የተጫወተ ሰው ነበር::

አኪውነስ እምነትና አመክንዮ የተጣመሩ መሆናቸውን ያምናል:: ሁለቱ እንደማይነጣጠሉ ሲያመላክትም«እምነት አመክንዮን ይጠቀማል:: አመክንዮም እውነትን ያለ እምነት ፈልጎ ሊያገኘው አይችልም::»[29] አመክንዮ የራሱ የሆኑ የሚገድቡት ባሕርያት ቢኖሩትም እንኳ፤ ከጠቀሜታው አኳያ በአኪውነስ እይታ አዎንታዊ የሆነ ስፍራ አለው:: በተለይም አኪውነስ የአመክንዮና የእምነት ግንኙነት ሁለቱም ነገሮች በየራሳቸው መንገድ ለሃይማኖት እምነት አስተዋጽኦ አበርካች እንደ ሆኑ በማሳየት ረገድ የላቀ ሥራ ሠርቶአል:: ለምሳሌ ለአኪውነስ እምነት ተገቢ ያልሆነ ነገር አይደለም፤ እምነት ከስምምነት ጋር የሚደረግ አመክንዮአዊ ሂደት እንጂ::»[30] አኪውነስ አክሎ እምነትን በተሻለ መልኩ ሲተነትን፣ «እምነት ከሳይንስ የሚለየው ባለቤቱ የማይታይ በመሆኑ ነው:: በተጨማሪም እምነት ካለማመን፣ ከጥርጣሬ እና ከግምታዊ አመለካከት የሚለየው እምነትን ለመደገፍ መረጃ በመኖሩ ነው::»[31] በአኪውነስ ግንዛቤ እምነት ባዶ በሆነ መሠረት የለሽ ነገር ላይ የሚደገፍ እንዳልሆነ ለማስተዋል

አይቸግርም:: ስለዚህ እምነት ፊት ለፊት በሚታይ ነገር ላይ የሚደረግ ተስፋ እንኳ ባይሆንም «አመክንዮአዊ እውነት ከክርስቲያን ሃይማኖት እውነት ጋር የሚቃረን አይደለም»[32] አኪውነስም ልክ እንደ አውግስጢኖስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣንነት አጽንኦት ሰጥቶ ይናገራል:: የነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር መገለጥ መሆናቸው የተመሠረተው በተፈጸሙ ትንቢቶችና ተአምራቶች ላይ ነው የሚል ሃሳብም ነበረው:: ስለዚህ «በአመክንዮ ብቻ ሊፈቱ የማይችሉ ነገሮች በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንነት ሥር በእምነት ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ»[33] ይህ ደግሞ እንደ ሥላሴ፣ ተሠግዎ (Incarnation) የመሳሰሉትን አስተምህሮዎን ያጠቃልላል:: እነዚህ አስተምህሮዎች አመክንዮን በመጠቀም የምንረዳቸው ገጽታዎች ቢኖሩዋቸውም፣ አመክንዮን የሚያልፉ ገጽታዎች ደግሞ አሉዋቸው::

አኪውነስ አመክንዮን የእምነት ጠላት ሳይሆን፣ አጋዥ እንደ ሆነ ነው የሚረዳው:: በአመክንዮ ብቻ የማንረዳቸው ነገሮች ስላሉ፤ እምነት ደግሞ አስፈላጊ ነው:: ይህም አኪውነስ ከጽንፈኝነት የፀዳ አቋምና አካሄድ እንዳለው እንድንገነዘብ



ይረዳናል:: በሌላ አነጋገር እምነት ከሌለ አመክንዮ ብቻ ሊጠቀመን አይችልም:: አመክንዮም ከሌለ እምነት ብቻ በራሱ የአመክንዮን ሚና ሊጫወት አይችልም:: ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ አኪውነስ እንደተናገረው « . . . መለኮታዊ ነባሬን (beings) በተመለከተ ሁለት እውነቶች አሉ፤ አንዱ በአመክንዮ የሚደረስበት ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ከሰው አመክንዮአዊ ችሎታ የሚያልፍ ነው:: ሁለቱም መንገዶች በመለኮታዊ መንገድ ሰው እንዲያምን ሊቀርቡለት የሚችሉ ናቸው»[34]:: ሆኖም ነገሮችን ያለ እምነት ተሳትፎ በሰው አመክንዮ ብቻ በመጠየቅ ለመረዳት መሞከር የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው አኪውነስ በሦስት ምክንያቶች አስደግፎ ይገልጻል::

«1. ጥቂት ሰዎች ብቻ ስለ እግዚአብሔር ይረዳሉ::

2. ከብዙ ጊዜ ልፋት በኋላ እንኳ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት በጣም በጥቂቱ ሊያገኙ ይችላሉ::

3. የሰው አመክንዮ ከስሕተት የጸዳ አይደለም:: ይህም ነገሮችን አመዛዝኖ የመፍረድ ዕውቀት ብቃት

ማነስና የብዙ ነገሮች መቀላቀል ነው»[35]

ይህን የምናውቅበት መንገድ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጅ በኀጢአት ከመውደቁ የተነሣ አመክንዮው እንደተበከለ ስለሚነግሩን ነው::

«እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: ያለ እምነት ደግሞ ማንም ቢሆን ሊያምን አይችልም::»[36] ይህም ሆኖ ግን በአኪውነስ ግንዛቤ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑ «የሚያምነውን ሰው ግንዛቤ በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ ያመናቸውን ነገሮች እንዳያስተያይ ወይም ነገሮችን ማመዛዘን እንዳይችል አያደርገውም::»[37] ከዚህ አቋም የተነሣ አኪውነስ ሲናገር እንዲህ ይላል:- «የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንነተ ተቀባይነት ካገኘ፤ አመክንዮን ተጠቅመን ስለ እምነት የምንለው ሊኖረን ይችላል:: ከአይሁዶች ጋር ለመከራከር ብሉይ ኪዳንን ልንጠቀም እንችላለን:: ከመናፍቃን ጋር ለመከራከር ደግሞ አዲስ ኪዳን ልንጠቀም እንችላለን:: ነገር ግን አሕዛብና መሐመዳውያን ብሉይ ኪዳንንም ሆነ አዲስ ኪዳንን አይቀበሉም:: ስለዚህ ሰዎች ሁሉ ስምምነታቸውን ሊሰጡት ወደሚገደዱት ወደ ተፈጥሮ አመክንዮ (Natural reason) መመለስ ይገባናል::»[38]



ይህ ተፈጥሮአዊ አመክንዮ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በሙሉ የሰጣቸው የማሰብና ከዚህም የተነሳ ነገሮችን የመገምገም፣ የማመዛዘን በመጨረሻም አንድ ዓይነት ድምዳሜ ላይ የመድረስ ብቃት/ ችሎታ ነው:: ይህም ችሎታ የሰው ልጆች የጋራ የሆነ መለያቸው ነው::

እስከ አሁን አጠር ባለ መልኩ ካነበብነው መመልከት እንደሚቻለው ከሆነ፣ አኪውነስ እምነትና አመክንዮን በሚመለከት ያለው አቋም ሚዛኑን የጠበቀ ነው:: ሁሉ ነገር በአመክንዮ ብቻ የሚፈታ እንኳ ባይሆን በእምነት ለምንቀበላቸው አመክንዮን ለሚያልፉ እውነቶች ትርጉምና ተቀባይነት፣ አመክንዮ አስፈላጊ እንደ ሆነ ያስገነዝበናል:

## <u>ማርቲን ሉተር Martin Luther (1483-1546 ዓ.ም)</u>

የ16ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ መሪ የሆነው፣ ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር፣ በአመክንዮ ላይ ያለው አመለካከት ጠንከር የሚልበት አቅጣጫ አለው:: ሉተር እምነት ለድነት (Salvation) በቂ መሆኑን ያለ ምንም ቅድሚያ ሁኔታ የሚያምን ሰው ነው:: «ጽድቅ በእምነት ብቻ» የሚለውም ሐረግ የሉተር ቁልፍ መታወቂያው

ነው:: ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት መመሥረት ያለበት በእምነት ላይ ነው:: እንደ ሉተር አባባል ያለ እምነት የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን አይቻልም::

ሉተር በእምነት ላይ ካለው አመለካከት ይልቅ ስለ አመክንዮ ያለውን አመለካከት ብዙዎች በተሳሳተ መልኩ እንዲረዱት በር ከፍቶአል:: ለምሳሌ «በአብዛኛዎቹ በጻፋቸው ጽሑፎቹ አመክንዮን «ሥጋዊ» «ደደብ» «አውሬ» የእግዚአብሔር «ጠላት» እና «የአታላይነት» ምንጭ እንደ ሆነ ይናገራል»[39] ሉተር በአመክንዮ ላይ ያለው አመለካከት በይበልጥ በአሉታዊ መልኩ እንዲታይ አስተዋጽኦ ያደረገው ተጨማሪ ምክንያት አመክንዮን ንጹሕ ሰውን የሚዳራ «ሴተኛ አዳሪ» ብሎ መጥራቱ ብቻ ሳይሆን፣ ግሪካዊውን ፈላስፋ አርስጣጣሊስን (Aristotle) በቃላት መወረፉም ጭምር ነው:: ይኸውም በሉተር ዐይኖች ፊት አርስጣጣሊስ «የቅዱስ አስተምህሮ አውዳሚ ጥራዝ ነጠቅ፣ «ዐዋቂና ጫሪ»፣ «የተረት ተረት ፈጣሪ»፣ «ቅድስና የጐደለው፤ የአደባባይ የእውነት ጠላት»፣ «የሚገማ ፈላስፋ»፣ «የመለስተኛና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትርኢት ሰው»፣ «አታላይ»፣ «ባለጌ» «ቀጣፊና



ታማኝነት የጐደለው»፣ «የአሕዛብ አውሬ»[40] በሚል መገለጹ ነው::

ማንም ሰው ቀደም ሲል ከላይ የተቀመጡትን አሳቦች ያነበበ ሰው ሉተር በአመክንዮ ላይ ባለው አመለካከት ላይ ጽንፍ መያዙ አይቀርም:: ምን አልባትም ሉተር በጣም ጠንከር ያሉ ቃላቶችን መጠቀሙ አርስጣጣሊስን የነቀፈውን ያህል እሱኑ መልሶ ሊያስነቅፈው እንደሚችል ሊያሳስብ ይችላል:: ይህን ያህል በአርስጣጣሊስ ላይ ነቀፋ የሰነዘረው አርስጣጣሊስ እምነትና አመክንዮ እንዲጣመሩ የሚያስችላቸውን የሥነ አመክንዮን መዋቅር የዘረጋ ፈላስፋ በመሆኑ ነው:: የአርስጣጣሊስን የሥነ-አመክንዮ መዋቅር በተመለከተ አጠር ያለ መግለጫ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12 ይመልከቱ:: ለምሳሌ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ፍልስፍናና ክርስትና የተጣመሩበት ዘመን ነበር:: እምነትና ክርስትና መጣመራቸው አመክንዮን የእምነት የበላይ እንዲሆን በር ስለከፈተ ማርቲን ሉተር ይህንን አጥብቆ ይቃወም ስለነበረ አርስጣጣሊስንም ጨምሮ ሊቃወም ችሏል:: ይህ በመካከለኛው ዘመን እምነትና የግሪክ ፍልስፍና የተጣመሩበት ሂደት ተምህሮነት (Scholasticism) ይባላል:: ለበለጠ ማብራሪያ የግርጌን

ማስታወሻ ቁጥር 40 ይመልከቱ:: ሉተር እጅግ በጣም በእምነት ላይ የሚያተኩር ሰው በመሆኑ አመክንዮ በክርስቲያናዊ እምነት ላይ ጫና ማሳደር የለበትም የሚል ጠንካራ አቋም የነበረው ሰው ነው:: በመሆኑም የክርስትና እምነት የግሪካውያንን ፍልስፍና ጥምረት ተቃወመ:: በሌላ በኩል በዚህ የጥምረት ሥራ ቶማስ አኪውነስና አውግስጢኖስ የተሳተፉበት ነበር:: ለምሳሌ ቶማስ የአርስጣጣሊስን ፍልስፍና በመጠቀም ከክርስትና እምነት ጋር አገናኝቶ በርካታ አስተምህሮን ገልጾአል:: እንደዚሁም ደግሞ አውግስጢኖስ የአፍላጦንን (Plato) ፍልስፍና በመጠቀም ስለ ክርስቲያናዊ እምነት ምንነት ግንዛቤውን አካፍሏል:: በሉተር አጽንኦት መሠረት ግን ድነት (Salvation) የእምነት ውጤት በመሆኑ ስፍራ ሊሰጠው የሚገባው ከስነ አመክንዮ በላይ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: በተምህሮነት መንገድ ከተሄደ ግን እንደ ሉተር ግንዛቤ የእምነትን ዋጋ የሚያሳጣው በመሆኑ የአርስጣጣሊስ አመክንዮ ደግሞ ይህን የሚደግፍ እንደሆነ ስላሰበ ተቃወመው::

እንግዲህ ወደ የትኛውም ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት ሉተር በአመክንዮ ላይ ያለውን አቋም በተለያዩ ደረጃዎች ማየት የተሻለ ስለሚሆን በሉተር



ነገረ መለኮት (Theology) ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ያደረገው ሰው ቢ.ኤ. ጌሬሽ (B.A Gerrish) ሉተር በአመክንዮ ላይ ያለውን አመለካከት ለመረዳት ከሦስት አቅጣጫዎች አመክንዮን ማየት እንደሚኖርብን ይጠቁመናል:: ሉተር አመክንዮን የሚጠቀመው በተለያዩ መንገዶች ነው::

«1. የተፈጥሮ አመክንዮ፣ በተገቢው ክልል ሲንቀሳቀስ፣

2. አመክንዮ የተፈጥሮ ወሰን ሲጥስ፣

3. ከመንፈሳዊ ጉዳዮች ጋር የተገናኘ ዳግም የተወለደ አመክንዮ ነገር ግን ዘወትር ለቃሉ የሚገዛ::»[41] ሉተር አመክንዮን የጠላው በሁለተኛው ዐይነት መንገድ አመክንዮ ጥቅም ላይ በመዋሉ ነው::ይህም ማለት ሉተር አመክንዮ የተፈጥሮን ወሰን ጥሶ በእምነት ላይ መሰልጠኑ አይዋጥለትም:: የተቀሩት የአመክንዮ መንገዶች ግን ይቀበላል::[42] ስለዚህ ሉተርን የአመክንዮ አጠቃቀም በሚገባ ለማወቅ ከጠቀሱት በየትኛው መንገድ አሳቡን እየገለጸ እንዳለ መረዳት የግድ ይላል:: ይህ ካልሆነ ግን ትችታችን ተገቢ አይሆንም:: በተጨማሪ ደግሞ ሙግታችን የተፋለሰ ይሆናል:: በጥቅሉ ሉተር በእምነት ይ

ያለው አቋም በጣም ጥብቅ በመሆኑ፣ በአመክንዮ ላይ ጥንቃቄ የተሞላበትን ጊስ ሲሰነዝር ይስተዋላል:: ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ ግን ሉተር የአመክንዮ ተጻራሪ አለመሆኑ ዕውቁ ፈላስፋ ዊሊያም ክሬግ ባስቀመጠው አጥርጥር (Summary) ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን:: «ማርቲን ሉተር በትክክል አለቃዊና አገልጋያዊ የአመክንዮ ጥቅም በማለት ለይቶአል:: በዚህም አለቃዊው አመክንዮ ጥቅም ላይ የሚውለው አመክንዮ በወንጌል ላይና አልፎ ተርፎም ልክ እንደ አለቃ ቆሞ ወንጌልን በሙግትና በመረጃ መሠረት ላይ ሲፈርድ ነው:: አገልጋያዊ አመክንዮ ጥቅም ላይ የሚውለው ደግሞ አመክንዮ ለወንጌል ሲገዛና ሲያገለግለው ነው::»[43] ብሎ ያምናል::

ስለዚህ ሉተር በደፈናው የአመክንዮ ተጻራሪ ተደርጎ ከመወሰዱ በፊት፤ ሉተር የአመክንዮ ተገቢ ባልሆነ መንገድ በሥራ ላይ መዋል ተቃዋሚ ወይስ በጭፍን አመክንዮን የሚጠላ ሰው ነው? የሚል ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል:: ሉተር የመጀመሪያውን አሳብ ማለት አመክንዮን ያለ አግባብ በሥራ ላይ መዋል አይቀበልም:: አመክንዮ ለእምነት የአገልጋይነት አገልግሎት የሚሰጠው ከሆነ በሉተር እይታ



እምነትና አመክንዮ የእጅና የጓንት ወዳጅነት ይኖራቸዋል ማለት ነው::

**ጆን ካልቪን John Calvin (1509-1564ዓ.ም)**

ካልቪን በ16ኛው ክፍለ ዘመን ተነስቶ የነበረውን የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ካስፋፉ አንቱ የተባሉ ቁልፍ ሰዎች አንዱ ነው::

ካልቪን በእምነትና በአመክንዮ ላይ ያለውን አመለካከት ለመረዳት፣ መሠረታዊ ከሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮዎች መነሣት የግድ ነው::ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር በዚህ ስፍራ ሊዳሰስ ስለማይችል አንኳር የሆኑ ጥቂት አሳቦችን ብቻ እንቃኛለን:: ካልቪን አጽንኦት ሰጥቶ ከሚያነሣቸው አሳቦች ውስጥ የ«እግዚአብሔር ዕውቀት አስተ ምህሮ» (the doctrine of the Knowledge of God) አንዱና መሠረታዊ የካልቪን ትምህርት አካል ነው::

ካልቪን ሰው ፈጣሪውን እንዲያውቅ ተደርጎ መፈጠሩን ይናገራል:: እንዲያውም «በሰው አእምሮ በተፈጥሮ መለኮታዊ ኃይልን ማወቅ አለ»[44] ይላል::እንደዚህ ሰው አባባል ለሰው ልጅ የፈጣሪን መኖር እንዲያስተውል ሌላው አጋዥ ነገር ቢኖር ፍጥረት ነው:: ይህን ነገር ካልቪን እንዲህ በማለት

ይገልጸዋል:: «እግዚአብሔር ራሱን በፈጠረው ዓለም ገልጦአል:: ቀን በቀን ደግሞ ራሱን ያሳያል:: በመሆኑም ሰዎች በሠራው ሥራ እርሱን ሳያዩ ዓይናቸውን መግለጥ አይችሉም::»[45] ከዚህ አሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለካልቪን ስለ ፈጣሪ ለማወቅ የመጀመሪያ ደረጃ የፈጣሪን የእጆቹን ሥራ ማየት መሆኑን ነው:: ይህም ከመዝሙረኛው አሳብ ጋር መጣጣሙን ልብ ይሏል:- "ሰማያትም የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል፣ ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች ፣ ሌሊትም እውቀትን ትናገራለች::" (መዝ. 19፣1-2):: ይህ እውነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን ሰው በተፈጥሮ ዕውቀት ብቻ ሊድን እንደማይችል ካልቪን ሳይጠቅስ አላለፈም:: የተፈጥሮ ዕውቀት ጥቅም ለሰው ልጅ የፈጣሪውን መኖር ጠቋሚ እንደ መሆኑ ሰው ላለማመን የሚያመካኝበት ነገር እንዲያጣ የሚያደርገው ነው:: ስለዚህ ሰው ወደ ሙሉና ወደሚያድነው ዕውቀት እስካልመጣ ድረስ ድነት አያገኝም:: ካልቪን ስለ ድነት ዕውቀት ሲናገር ጠበብ አድርጎ የሚያሳየን ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አስፈላጊነት ነው:: «ምንም እንኳ ላለማመን የምናመካኝበትን ነገር እንድናጣ የእግዚአብሔር



የክብሩ ግርማ በፍጥረቱ የተገለጠ ቢሆንም፤ ፈጣሪያችንን በሚገባ ለማወቅ ተጨማሪና የተሻለ ረዳት ያስፈልገናል:: ከዚህ የተነሣ ራሱን በቅርበት ለገለጠላቸው ሰዎች የቃሉን ብርሃን በላያቸው ላይ እንደ ልዩ ዕድል አብርቶላቸዋል... ቅዱሳት መጻሕፍት የተምታታውን በአእምሮአችን ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ዕውቀት ግልጽ ያደርጉልናል:: እርሱንም [እግዚአብሔርን] በተለየ መልኩ ይገልጡልናል::»[46] ከተፈጠሩ ነገሮች ስለ እግዚአብሔር ልናገኝ የምንችለው ዕውቀት እውነት ሆኖ እያለ ግን ካልቪን እንደ ገና ሲመክረን፣ «ሰው ስለፈጣሪው በማወቅ ጥሩ ርምጃ ወደ ፊት መጓዝ ከፈለገ ጆሮዎቹን ለእግዚአብሔር ቃል መስጠት አለበት:: ማንም ሰው ቢሆን የቅዱሳት መጻሕ ፍት ተማሪ ካልሆነ በጣም አናሳ (ዝቅተኛ) የሚባልለትን የትክክለኛና የጤናማ አስተምህሮ ጣዕም እንኳ ሊያገኝ አይችልም::»[47] ካልቪን ለቅዱሳት መጻሕፍት የላቀ ስፍራ የሚሰጥ ቢሆንም እንኳ ተአማኒነታቸውን ግን ለማረጋገጥ የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ወይም የሰውን አመክንዮ ሳይሆን የሚያነሣው የመንፈስ ቅዱስን ውስጣዊ ምስክርነትን ያስቀድማል ቃል በቃልም እንዲህ

ይላል፡- «ቅዱሳት መጻሕፍት ለእግዚአብሔር የድነት ዕውቀት በቂ ናቸው:: ይህም እውን ሊሆን የሚችለው ውስጣዊ በሆነ በሚያሳምን በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ብቻ ነው::»[48] እንግዲህ ካልቪን ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ፍጥረት አስፈላጊ መሆኑን ቢያምንም ለድነት ዕውቀት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስፈልጉት ያሰምርበታል:: ስለዚህ በካልቪን አካሄድ የእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ተአማኒነት የሚረጋገጠው በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ብቻ ከሆነ፣ ስለ እምነትና አመክንዮ ምን ዐይነት አመለካከት እንዳለው አሁን መጠየቅ እንችላለን:: እስቲ ቀድመን አንደኛውን ገጽታ እንመልከት- እምነትን::

ካልቪን እምነት ምን እንደ ሆነ ሲናገር፣ «እምነት ጽኑና ተአማኒነት ያለው ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ዕውቀት ነው:: ይህም ዕውቀት የተመሠረተው ለግንዛቤአችን ይሆን ዘንድ በክርስቶስ በኩል በተገለጠው በጸጋው ተስፋ እውነት ላይ ነው:: እውነቱም በልባችን ላይ በመንፈስ ቅዱስ ታትሞአል::»[49] ለካልቪን የእምነት መሠረት አመክንዮ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ «እምነት በጥቂቱ እንኳ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ከተፋታ /ከተላለፈ/ ተፈ ጥሮውን ያጣዋል፤ ውጤቱም ግልብ እምነትና ስሕተት ይሆናል:: ቃሉ የእምነት መሠረት ነው፤ ቃሉ በሌለበት እምነት አይኖርም::»[50]

እምነት ትርጉም እንዳለው ካልቪን ያምናል፤ ሆኖም ግን ለእርሱ የእምነታችን መሠረት የእግዚአብ ሔር ቃል ነው:: የእምነትን ይዘት ልናገኝ የምንችለው ከቃሉ ይሆናል:: ስለዚህ እምነት ከእግዚአብሔር ከራሱ ዘንድ የሚሆንልን ነገር እንደ ሆነ መረዳት እንችላለን:: በመሆኑም «. . . ትክክለኛ እምነት በራሳችን ጥረት ማግኘት አንችልም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ስለ ልጅነታችን መብት በሚመሰክርልን ጸጋ ነው::»[51] በካልቪን እይታ የእምነት ምንጭ እግዚአብሔር ይሁን እንጂ፣ «የእምነት መገለጫው ስንፍና ሳይሆን የእግዚአብሔር ዕውቀትና ፈቃዱ ነው::»[52]

ሁለተኛው ገጽታ አመክንዮ ነው:: የካልቪን እምነት ሙሉ በሙሉ የተያያዘው ከእግዚአብሔር ጋር ነው የሚለው አተያይ፣ ሰው የራሱን አመክንዮ በመጠቀም ሊያከናውናቸው የሚችላቸው ነገሮች የሉም ማለት ነው? የሚል ጥያቄ ሊፈጥር ይችላል::

ካልቪን የሰው አመክንዮ ከእምነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የበኩሉን ሚና ሊጫወት እንደሚችል የሚረዳው ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ነው:: ይህ በመሆኑ ካልቪን ሲናገር፣ «ሰው ደግና ክፉ ነገርን የሚለይበት፣ ነገሮችን የሚረዳበትና የሚፈርድበት የአመክንዮ ኀይል የተፈጥሮ ስጦታ ነው:: ስለዚህ አመክንዮ ሙሉ ለሙሉ የተደመሰሰ አይደለም::»[53]

ካልቪን የሰው አእምሮ ከኀጢአት የተነሣ ስለተበላሸ አመክንዮ በራሱ የእግዚአብሔርን እውነት እንድንረዳ የሚያግዘን ዋና መንገድ አይደለም የሚል አቋም አለው:: ይህ ማለት ግን አመክንዮ ሙሉ ለሙሉ ፋይዳ ቢስ ነው ማለት አይደለም:: «በእርግጥ ለማያምኑ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ለማረጋገጥ መሞከር ትርጉም የለሽ ነው:: ይህም በእምነት ብቻ የሚታወቅ በመሆኑ ነው::»[54] «ምንም እንኳን አንድ ሰው ውጤታማ በሆነ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ከተቃዋሚዎች ጥቃት ሊታደግ ቢሞክር ያ ሰው በተ ቃዋሚዎች ልብ ውስጥ ከእግዚአብሔር የሆነ ትክክለኛ እምነት ሊመሠርት አይችልም::»[55] በዚህ ረገድ ካልቪን የአመክንዮ ተቃዋሚ ሳይሆን የአመክንዮን የእምነት ነገር በመረዳት ረገድ ያለውን



ብቃትና ውሱንነት ገላጭ ነው:: «በራሳቸው መረጃ ዎች ጽኑ እምነት ሊያመጡ አይችሉም:: ይህም የሰማዩ አባት ግርማውን በዚያ ቦታ እስኪገልጥ፣ ለቅዱሳት መጻሕፍት ከክርክር ያለፈ አክብሮት እስኪያመጣ ድረስ ነው::»[56]

በአጭሩ የካልቪን አካሄድ የሰው አመክንዮ በእምነት ጉዳይ ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትና የመንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ምስክርነት ያህል ሰውን የማሳመንም ይሁን የመለወጥ ኃይል የለውም:: ሆኖም ግን አመክንዮ ከእምነት ጋር የተፋታ ነገር አይደለም:: ለማንኛውም ካልቪን ስለ ራሱ በተናገረው ሀሳቡን እንቋጭ:-

«በራሴ በኩል ታላቅ ክህሎት ወይም አንደበተ ርቱዕነትን ባልጎናጸፍም እንኳ፣ እግዚአብሔርን የሚንቁትን፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በብልጠታቸውና በቀልዳቸው ሊያብጠለጥሉ የሚፈልጉትን ሰዎች ክርክር መግጠም ካለብኝ፤ ልቅ አፋቸውን በቀላሉ ጸጥ ለማሰኘት ወኔው አለኝ::»[57]

## <u>ብሌዝ ፓስካል Blaise Pascal (1623-1662 ዓ.ም)</u>

በ17ኛው ክፍለ ዘመን በፈረንሳይ አገር ተወ ልዶ የነበረ የሂሳብ ሊቅ ፈላስፋና የፈጠራ ሰው

ነው::

ፓስካል ስለ አመክንዮና እምነት ያለው አመለካከት ከዚህ ቀደም ካየናቸው ሰዎች ጋር የሚመሳሰል ነው:: እናም እንደዚህ ሊቅ አባባል ሰው ትልቅ ነው:: ሰው ከኃጢአት የተነሣ ደግሞ የትልቅነቱን ማዕረግ ሊያጣ የበቃ ፍጡር ነው:: የሆነ ሆኖ ግን የሰው ተፈጥሮ የሚያስደንቅ ገጽታ አለው:: ሰው ስለ ራሱ የሚኖረው እይታ ሚዛናዊ የሚሆነው የኃይለኛነቱን ያህል ደካማ ማንነቱን ዐውቆ ሲኖር ነው:: ፓስካል በይፋ እንደ ተናገረው «እኛ በትዕቢት፣ በምኞት፣ በፍትወት፣ በድካም፣ በችግር እና ፍትሕን በማጓደል እንደ ተሞላን ካላወቅን ዕውራን ነን::»[58] ይህ ብቻ አይደለም:: ፓስካል ስለ ሰው ኃጢአተኛነት ሲናገር ሰው በራሱ ችሎታ ከገባበት ችግር ነጻ ሊወጣ አይችልም ይላል:: ለዚህም ነጻ የሚያወጣውን ፈጣሪውን በእምነት ሊገናኘው የግድ እንደ ሆነም አጽንኦት ሰጥቶ ይናገራል:: ቀጥሎም ከዚህ የተነሣ፣ ሰው ችግር ውስጥ እንዳለ ዘንግቶ ስለ እግዚአብሔር የሚኖረው ዕውቀት ትዕቢት ያስከትላል:: ፓስካል ወደ መፍትሔ ሲመጣም እንዲህ ይላል፡- ሰው ያለ እግዚአብሔር ደግሞ ስለ ራሱ ችግርና ድካም ማወቁ ተስፋ መቁረጥን



ያመጣል:: ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማወቁ ሚዛኑን የጠበቀ ዕውቀት እንዲኖረው ያደርጋል፤ ምክንያቱም በእርሱ [በክርስቶስ] በኩል እግዚአብሔርንም ድካሙንም ማግኘትና ማወቅ ስለሚችል ነው::»[59] በሌላ አነጋገር ክርስቶስን ባወቅን መጠን ስለ ራሳችን ትክክለኛ ግንዛቤ እንጨብጣለን:: ከዚያም ባሻገር ስለ እግዚአብሔር ያለን ዕውቀት ያለ ክርስቶስ የተሟላ አይሆንም ማለት ነው:: ስለዚህ ለሰው ልጅ ክርስቶስን ማወቅ ወሳኝ ነው::

ፓስካል ስለ ሰው ያለው አመለካከት ሰው ከኃጢአተኛነቱ የተነሣ ባሕርይው እክል እንደገጠመው ያመለክታል:: ይህ ደግሞ በሰው እምነትና አመክንዮ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ መኖሩ አይቀሬ ነው:: እምነት ለፓስካል «ከማመን ርምጃ ወይም ወደ ክርስቶስ ለድነት ከሚደረግ ጥሪ ይበልጣል:: ይልቁንስ እምነት ሕያው ሂደት፣ ረጅምና በሥርዐት የተካነ የሕይወት ዘመን ፍቅር፣ ለውጥ እና የተሰጠ የክርስቲያን ባሕርይ ነው::»[60] ከዚህም ባሻገር እምነት ለፓስካል፣ «ከማረጋገጫ (Evidence) ይለያል፤ አንዱ ምድራዊ (ሰዋዊ) ነው፣ ሌላው (እምነት) የእግዚአብሔር ስጦታ ነው...

ይህ በሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስቀምጠው እምነት ነው። ማረጋገጫ ግን ሁል ጊዜ መሣሪያ (tool) ነው።»[61] ፓስካል ለእምነት የሚሰጠው ስፍራ ለአመክንዮ ከሚሰጠው የላቀ ነው። በመሆኑም «ልብ አመክንዮ የማያውቀው የራሱ የሆኑ እውነቶች አሉት ይላል።»[62] አንዳንድ ሰዎች ፓስካል በአመክንዮ የማያምን እምነታዊ (Fidiest) እንደ ሆነ ያስባሉ። ይህ አመለካከት ግን ልክ አይደለም። ምክንያቱም ፓስካል በጽሑፎቹ የአመክንዮን ውሱንነት እንጂ፣ አመክንዮን በጅምላ እንደማያምን ስለማይናገር ነው። ፓስካል ስለ ሰው ሲናገር እንኳ «በግልጽ ሰው የተፈጠረው ለማሰብ ነው፣ ይህም ሙሉ ክብሩና ግዴታው ነው። ግዴታውም እንደሚገባው ማሰብ ነው።»[63]ይላል። ሰው ማሰብ ያለበት እንዳሻው ሳይሆን፣ የአመክንዮን ገደብ ወይም ውሱንነት በማወቅ ነው። «የአመክንዮ የመጨረሻ ደረጃ ከዐቅሙ በላይ የሚሆኑና የሚያልፉ ስፍር ቊጥር የሌላቸው ነገሮች እንዳሉ ማወቅ ነው።»[64]

ለፓስካል ሃይማኖታዊ እውነትን ለማወቅ፤ ሰው ወደ መለኮታዊ መገለጥ መምጣት እንዳለበት ግልጽ ቢሆንም እንኳ፤ የእምነትና የአመክንዮ ሚዛን መጠበቅ አለበት። «ሁሉን ነገር ለአመክንዮ በናስገዛ



ሃይማኖታችን ያለ ምንም ምስጢራዊና ተአምራታዊ (ልዕለ ተፈጥሮአዊ ክሥተቶች) ይቀራል፤ የአመክንዮንም መርሖች ብንጥስ ደግሞ ሃይማኖታችን ትርጉም የለሽና እርባና ቢስ ይሆናል።»[65] በሌላ አገላለጽ ለፓስካል አመክንዮና እምነት በየራሳቸው መንገድ ጠቃሚ ናቸው። በመሆኑም አመክንዮና እምነት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ከተፈለገ ጥቅማቸው ሊታወቅ ይገባል። አንዱ የሚሰጠው ጥቅም በሌላኛው ወገን ስለማይተካ ከሁለቱም ሊገኝ የሚችል ጥቅም ለሃይማኖታዊ እምነት የተሟላ ገጽታ ይሰጠዋል።

ፓስካል እምነትና አመክንዮ በየራሳቸው አቅጣጫ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ እንደ ሆኑ ይናገራል። ሆኖም ግን፣ «አመክንዮ የእምነትን ያህል ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሕይወት ምንነት እንድናውቅ አያስችለንም። ይህም በእምነት ሊገኝ የሚችል ዕውቀት በመሆኑ ነው። እግዚአብሔርን ሊለማመድ የሚችለው ልብ በመሆኑ ልብን ደግሞ በአመክንዮ መድረስ አንችልም።»[66] በፓስካል እይታ የአመክንዮን ገደብ መረዳት ከሰው ከራሱ ማንነት ውሱንነት ጋር የተገናኘ እንደሆነ ማየት እንችላለን። ይህ ደግሞ የፓስካልን የአመክንዮ ተጻራሪ መሆኑን

ሳይሆን ልኩን (ገደቡን) ያወቀ እንደ ሆነ ያሳያል:: «የሰው አመክንዮ እንደ ፓስካል አመለካከት ሁል ጊዜ ውስን ነው:: ይህም የሆነው ሰዎች ስለ ታላላቅ መንፈሳዊ ጉዳዮች ለማወቅ በእግዚአብሔር መገለጥ እስካልተደገፉ ድረስ በዕውቀታቸው ውስን በመሆናቸው ነው::»[67] ፓስካል ሰው በራሱ ጥበብ ብቻ በመታገዝ የእግዚአብሔርን እውነት ማወቅ አዳጋች እንደሆነ በማመን የእግዚአብሔርን ዕርዳታ አማራጭ የሌለው ነገር አድርጎ ያቀርባል::

እንግዲህ ስናጠቃልል ፓስካል እምነትን ላቅ አድርጎ ይመለከተዋል:: አመክንዮን በሚመለከት ደግሞ እንዲህ ይላል፣ «ክርስትና የሚያስተምረውትሕትና አመክንዮን ለመለኮታዊ መገለጥ መገዛትን (Submit) ማድረግን ያካትታል::»[68] «መገዛትና አመክንዮን መጠቀም ልክ የሆነውን ክርስትና ይፈጥራል::»[69] አመክንዮ ትክክለኛ ተግባሩን ሊፈጽም የሚችለው፣ለእምነት ተገቢውን ሥፍራ በመስጠት ጥቅም ላይ ሲውል ነው:: ይህም የአመክንዮን ለእምነት መገዛት የተባለውን ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ያደርገዋል:: ፓስካል የእግዚአብሔርን ታላቅነት ከመረዳቱ የተነሳ ሰው ውሱን እንደሆነ ያምናል:: ያለ እምነት ደግሞ



በአመክንዮ ብቻ ስለ እግዚአብሔር ለመረዳት ሰው መልፋት እንደሌለበት ያስገነዝባል::

## የታሪካዊ ዳራ ግምገማ

ከአውግስጢኖስ እስከ ብሌዝ ፓስካል ያለው ጊዜ ሲታይ፣ እምነትና አመክንዮ የተጣመሩ (እርስ በእርሳቸው የማይጣረሱ) መሆናቸውን ልብ ይሏል:: የእነኚህ ታላላቅ የቤተክርስቲያን ታሪክ የጀርባ አጥንት የሆኑ ሰዎች እምነትና አመክንዮን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መረዳታቸው ለክርስቲያናዊ ሥነ-መለኮት መጎልበት ከፍተኛ መሠረት ጥሎ አልፎአል::

ለቅዱስ አውግስጢኖስ እምነትና አመክንዮ የተፋቱ ሳይሆኑ፣ ተጣምረው የየራሳቸውን ሚና የሚጫወቱና ለቅዱሳት መጻሕፍት ተገዥ መሆን ያለባቸው ነገሮች ናቸው:: ይህ ደግሞ አውግ ስጢኖስን ለእምነት ያለውን ላቅ ያለ ስፍራ አመልካች ነው:: ቶማስ አኪውነስ ደግሞ ከአውግ ስጢኖስ ጋር ሲስተያይ በእምነትና በአመክንዮ አቋሙ የሚያመሳስለው ሁለቱንም ነገሮች በሥራ ላይ ሊውሉና ላይውሉ የሚችሉበትን መንገዶች በማሳየት ረገድ ነው:: እምነት ከአመክንዮ

ስለሚያልፉ ነገሮች ረጂነቱ ከፍ ያለ መሆኑና አመክንዮ ደግሞ የእምነትን ዕርዳታ ሳንሻ ልንረዳቸው ለምንችላቸው ነገሮች የበኩሉን አስተ ዋፅኦ ማድረጉ መታመኑ ነው:: የሉተርን አቋም ስንቃኝ፣ ስለ እምነት ያለው አመለካከቱ ለአመክንዮ ካለው አመለካከቱ ላቅ ያለ ቢሆንም፣ አመክንዮን በተመለከተ ደግሞ ከአጠቃቀም የተነሣ የእምነትን መሠረት ሊያናጋ ስለሚችል፤ አመክንዮ ተቀባይነት ማግኘት የሚኖርበት ማጣሪያ ውስጥ ገብቶ ጤናማነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው:: ይህም አመክንዮ በእግዚአብሔር ቃል ሥር ያለ በመሆኑ ነው:: ከዚህ የተነሣ ደግሞ አመክንዮ የእምነት አገልጋይ ሊሆን ይገባል:: ይህም በሉተር አካሄድ አመክንዮ ከእምነት ጋር ቁርኝት የለውም ለማለት ሳይሆን፣ ከእምነት ጋር ያለውን ዝምድና ጠብቆ ሊዘልቅ የሚችለው ውሱን መሆኑ ታውቆ ያለቦታው በሥራ ላይ በማይውልበት ሁኔታ ብቻ ነው:: ወደ ካልቪን አቋም መለስ ስንል ደግሞ አመክንዮ ከሰው ኃጢአተኛነት የተነሣ ለጤናማነት ማጣት የተጋለጠ በመሆኑ፣ ያለ እምነት ጠቀሜታ አይኖረውም:: የኃጢአት ውጤት በአመክንዮ ላይ ያመጣው ጠባሳ በእምነት በኩል ሊቀረፍ ሲችል፣ ትልቁን ሚና



ሊጫወት የሚችለው ግን አሁንም እምነት ነው:: አመክንዮ ለካልቪን ውሱን ነው:: የብሌዝ ፓስካል አቋም የእስከ አሁኖቹን አቀራረብ የተከተለ ነው:: በመሆኑም ፓስካል አመክንዮ እምነትን ተከታይ እንጂ ቀዳሚ ሊሆን እንደማ ይገባው ይናገራል:: ሰው በኃጢአት የወደቀ በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ራሱና ስለ ፍጥረት በንጹሕ መንገድ ማሰብ የሚችለው አመክንዮው በእምነት ተገርቶ ከፈጣሪ ጋር ሰው በሚያደርገው የግል ግንኙነት ነው:: ስለዚህ ፓስካል አመክንዮ ውሱን ቢሆንም ከእምነት ጋር ተስማምቶ ሊያገለግል እንደሚችል ያምናል::

ስለዚህ በአውግስጢኖስ፣ በአኲውነስ፣ በሉተር፣ በካልቪንና በፓስካል መካከል ያለው የጋራ አቋም፣የአመክንዮና የእምነት ጥምረት እንደተጠበቀ ሆኖ የእምነት የበላይ መሆንና የአመክንዮ ውሱንነት ነው:: እነኚህ ሰዎች የአመክንዮን ውሱንነት ያጎሉት፤ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ውሱን ከመሆኑ የተነሳ ነው::በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለው ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ፍጡር ሁልጊዜ ፈጣሪው በሁሉ ነገር ኢ-ውሱን በሆነ መልኩ የላቀ እንደሆነ መረዳት ይኖርበታል:: ስለዚህ እምነት አመክንዮን ሳይጻረር፣

በአመክንዮ ቁጥጥር ሥር ደግሞ ሳይሆን አልፎት ሊሄድ እንደሚችል ግልጽ ሊሆን ይገባል::

«በተለይም የእምነትና የአመክንዮ መደጋገፍ በክርስትና እምነት ውስጥ ከ17ኛ ክፍለ ዘመን በፊትና በኋላ አንድ ዐይነት ገጽታ የለውም:: በ1650 እና 1850 ከስፒኖዛ እስከ ጀርመናዊው ለዘብተኛ የፕሮቴስታንት ነገረ መለኮት ጀማሪ ሽየርማከር ባለው ጊዜ ውስጥ አመክንዮአዊ የክርስቲያናዊ እምነት መሠረት ተለወጠ:: ከዚያ በፊት አመክንዮና እምነት አብረው መሥራት አይቸግራቸውም ነበር:: አመክንዮ ለእምነት መረጃ ያቀርብ ነበር:: ነገር ግን ከስፒኖዛ እስከ ሽየርማከር ባለው ጊዜ ውስጥ መረጃ አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ ክርስቲያናዊ እምነት ሊረዳ ይችላል የሚለው አሳብ ራሱ ተተወ»[70] ይህም ከመሆኑ የተነሣ በእምነትና በአመክንዮ ላይ የአመለካከት ልዩነቶች እየሰፉ መጡ:: ስለዚህ እምነትና አመክንዮ በተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ትርጓሜ የሚሰጧቸው ነገሮች ሆኑ:: ከእነዚህ አመለካከቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን በምዕራፍ ሶስት እንመለከታለን::[71]



# ምዕራፍ ሶስት

## እምነትና አመክንዮ በተለያዩ ሰዎች እይታ

እምነትና አመክንዮን አስመልክቶ ያሉት ምልከታዎች ብዙ ሲሆኑ፣ ዋና ዋና የሚባሉት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. መገለጥ ብቻ:- ከአመክንዮ ይልቅ ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ሊረዳን የሚችለው ልዩ መገለጥ (Revelation) ብቻ ነው:: ከዚህ ያለፈ ማንኛውም ዐይነት አመክንዮአዊ፣ መረጃዊ፣ ታሪካዊ የሆነ የእግዚአብሔርን ማንነት ለማወቅ የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከንቱ ነው:: በአመክንዮአዊ መንገድ መለኮታዊ እውነት ማወቅ ለሰው አእምሮ የሚቻለው ነገር አይደለም:: ሰው በኃጢአት የወደቀ እንደ መሆኑ፣ ከመለኮታዊ መገለጥ ውጭ እውነትን የሚያውቅበት መንገድ የለም:: በዚህም አመለካከት የዘመናዊው ህልውናነት (Existentialism) አባት የሆነው ሶረን ኪርክጋርድና የ20ኛው ምዕተ ዓመት ታላቅ

የነገረ መለኮት ሰው ካርል ባርት ይገኙበታል:: 20ኛው ምዕተ ዓመት ጀርመናዊው የአዲስ ኪዳን ሊቅ የሪዶልፍ ቡልትማን አመለካከት ከዚህ ብዙ አይርቅም:: ስለ ዘመናዊ ህልውናነት በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 71 ይመልከቱ::

2. <u>አመክንዮ ብቻ:-</u> ማንኛውም ከአመክንዮ ጋር የማይጣጣም ሀሳብ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም:: ከአመክንዮ ጋር አብሮ የማይሄድ አሳብ ታምራትም ይሁን ሌላ ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንኳ ቢገኝ ዕጣ ፈንታው መሆን ያለበት መጣል ነው:: እውነት የሆነ ነገር መለኪያው መሆን ያለበት አመክንዮ ነው:: አመክንዮ ለዕውቀታችን አስተማማኝ የሆነ ማረጋገጫ መንገድ ነው:: ስለ አንድ ነገር ርግጠኞች ለመሆን መደገፍ ያለብን በእምነት ላይ ሳይሆን በአመክንዮ ላይ ነው:: እምነት ከስህተት አያድንም:: እምነት አስተማማኝ የሆነ የዕውቀት በር አይደለም:: በመሆኑም አመክንዮ ብቻ ተቀባይነት ላለው እውቀት ትክክለኛ የመረጃ ምንጭ ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ በአመክንዮ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች በተወሰነ ደረጃ ብቻ ለእምነት ስፍራ ሰጥተዋል:: ይሁን እንጂ እምነት አሁንም አመክንዮን እስካገለገለ ብቻ ነው:: በዚህ አመለካከት ሥር የ18ኛው ክፍለ ዘመን ዕውቁ ፈላስፋ ኢማኑኤል ካንት በተወሰነ ደረጃ እምነት አመክንዮን ካገለገለ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል



ቢያምንም ሌላኛው የ17ኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፋ ስፒኖዛ ግን ሥር ነቀል የሆነ የአመክንዮአዊነት ብቻ ተቀባይ ነው:: በዚህ በአመክንዮ ብቻ አመለካከት ሥር ኢማኑኤል ካንትና ቤኒዲክት ስፒኖዛ ይገኙበታል::

3. <u>አመክንዮ በመገለጥ ላይ</u>:- መገለጥ (Revelation) አስፈላጊ ነው:: ሆኖም ግን አመክንዮ ከመገለጥ ይልቅ ተቀባይነት ያለው ነገር ነው:: መገለጥ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ አመክንዮ የሚያስገኘው ጥቅም የበለጠ ነው:: ከአመክንዮ ጋር ለሚጻረር ነገር ብዙ ስፍራ መስጠት አስፈላጊ አይሆንም:: መገለጥ ጥቅሙ ባይካድም፤ ጉልቶ መውጣት ያለበት አመክንዮ ነው:: በዚህ አመለካከት ሥር የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አበው መካከል ዮስጦስ ሰማዕትና ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ ይገኙበታል:: በተጨማሪ የዚህ አመለካከት ሁነኛ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ለዘብተኛ አቋም ያላቸው የነገረ መለኮት ሊቃውንት ናቸው:: ይህ ጎራ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ጣልቃ አይገባም ብለው የሚያምኑትን አምላከኛውያንን (Deists) ጭምር ያካትታል:: ስለ ለዘብተኝነት (Liberals) በግርጌ በቁጥር 71 ሥር አጠር ያለ ማብራሪያ ተሰጥቷል::

4. <u>መገለጥ በአመክንዮ</u> ላይ፡- መገለጥ በአመክንዮ ላይ የበላይነት አለው፡፡ አመክንዮ በመገለጥ ሥር እንጂ መገለጥ በአመክንዮ ሥር ሊሆን አይገባም፡፡ አመክንዮ ስፍራ ሊኖረው የሚችለው መገለጥን ሲከተል እንጂ ሲያስከትለው አይደለም፡፡ አመክንዮ በመገለጥ ላይ የተደገፈ እንጂ የአለቅነት ሚና አይጫወትም፡፡ በዚህ አመለካከት ሥር ጠርጡሊያኖስና ኮርነሊየስ ቫንቲል ይገኙበታል፡፡

5. <u>መገለጥና አመክንዮ</u>፡- እምነት ሰውን ወደ መረዳት ይመራዋል፡፡ ግንዛቤ ከእምነት የሚገኝ የአመክንዮ የጥረት ውጤት ነው፡፡ አመክንዮ የእግዚአብሔርን መኖር እንድናውቅ ያግዘናል ሆኖም በርካታ ከአመክንዮ ችሎታ ዐልፈው የሚሄዱ እውነቶች አሉ፡፡ እነኚህን አመክንዮን የሚያልፉ እውነቶች ደግሞ ልንረዳቸው /ልናውቃቸው/ የምንችለው በእምነት ነው፡፡ አመክንዮ ግን ስለምና ምናቸው እውነቶች ተገቢነት ግንዛቤ እንድንጨብጥ ያግዘናል፡፡ በዚህ በእምነትና አመክንዮ የጥምረት አገልግሎት አመለካከት ሥር ቅዱስ አውግስጢኖስና ቶማስ አኪውነስ ይገኙበታል፡፡ በእነኚህ በአምስቱም አመለካከቶች ሥር የተጠቀሱ ሰዎች ማንነት አጠር ባለ መልኩ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ተብራርቷል፡፡



## <u>ግምገማ</u>

ከላይ በታሪካዊ ዳራ ሥር ከተዘረዘሩት ከአምስቱ አመለካከቶች ውስጥ በአራቱ ላይ ብቻ እንነጋገራለን፡፡ አምስተኛው 'አመክንዮና መገለጥ' የሚለው አመለካከት ከላይ ከአውግስጢኖስ እስከ ብሌዝ ፓስካል ድረስ ካለው የእምነትና የአመክንዮ ድምዳሜ ጋር አንድ ዐይነት በመሆኑ ነው፡፡ ይህም አቋም እምነትና አመክንዮ የተፋቱ ነገሮች ሳይሆኑ የተጣመሩ ናቸው የሚል አቋም ነው፡፡ እንግዲህ መገለጥ ብቻ፣ አመክንዮ ብቻ፣ አመክንዮ በመገለጥ ላይና መገለጥ በአመክንዮ ላይ የሚሉትን አቋሞች ስናጠቃልል እያንዳንዱ አቋም በራሱ መንገድ በተ ወሰነ ደረጃ ሊያስሄድ የሚችል እውነት ቢኖረውም ደካማ ጐኖችም እንዳሉት ልብ ይሏል፡፡

### ሀ. መገለጥ ብቻ

መገለጥ ብቻ የሚለው የኪርክጋርድ፣ የባርትና የቡልትማን አመለካከት የአመክንዮን ከመገለጥ ጋር ያለውን ዝምድና የሚክድና መገለጥን የመጀመሪያም የመጨረሻም የእውነት ማወቂያ መንገድ አድርጎ የሚያስቀምጥ አካሄድ አለው፡፡ በርግጥ በአንድ ጐኑ መለኮታዊ እውነት በመገለጥ መታወቁ እውን ቢሆንም፣ ይህንኑ ለመረዳት ሥራ ላይ የዋለ አመክንዮ እርባና ቢስ እንደ ሆነ መታሰቡ

አመለካከቱን ኢ-ሙሉዕ ያደርገዋል:: ለምሳሌ:- አመክንዮ ጥቅም ላይ ሳይውል ይህን አቋም እንኳ መግለጽ አይቻልም::

## ለ. አመክንዮ ብቻ

አመክንዮን ብቻ የእውነት ተቀባይ መስፈርት በማድረግ የተነሣው የኢማኑኤል ካንትና ቤኒዲክት ስፒኖዛ አመለካከት፣ የመገለጥን አስፈላጊነት ከመካዱ፣ ባሻገር፣ ለአመክንዮ የማይገባውን የብቃት ማረጋገጫ ያስጨበጠ ነው:: የአመክንዮ ጥቅም ግልጽ ቢሆንም ሁሉ ነገር በአመክንዮ ብቻ ይፈታል ብሎ ማሰብ ከእውነት ውጭ ሊሆን የሚችል በመሆኑ፣ መገለጥ ብቻ ካሉት ከነ ባርት፣ ኪርክጋርድና ቡልትማን አካሄድ ጋር በጽንፈኝነቱ የሚመሳሰል ሆኖ፣ የአመክንዮን ውሱንነት ከግምት ውስጥ ያላስገባ ነው:: አመክንዮ ደግሞ ሊገልጻቸው ለማይችላቸው ነገሮች ደግሞ ምላሽ ሊሰጥ ብቃት ያንሰዋል:: ለምሳሌ:- እግዚአብሔር በባሕርይው አንድ ነው በአካል ሦስት ነው:: ሆኖም እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል:: ከዚህም የተነሣ ይህን እውነት ለማመን የመገለጥን አስፈላጊነት ለመቀበል የማይፈልግ ግትር አቋም ነው::



## ሐ. አመክንዮ በመገለጥ ላይ

አመክንዮ በመገለጥ ላይ የሚል የዮስጦስ ሰማዕትና የቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ አቋም አመክንዮን ከመገለጥ ገንጣይ ባይሆንም ሚዛኑን የጠበቀ አይደለም:: ይህም የሆነው መገለጥን በአመክንዮ ሥር በማድረግ ይገዛዋል:: በርግጥ በማወቅ ሥርዐት ውስጥ (knowing Order) አመክንዮ መገለጥን ሊቀድመው ይችላል:: ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ አመክንዮን መጠቀም የግድ ነውና:: በሥነ ኑባሬ ሥርዐት (Ontological Order) ግን መገለጥ አመክንዮን ስለሚቀድመው አመክንዮ የመገለጥ የበላይ ሆኖ የሚቀር ከሆነ፣ ውስንነቱ ተዘንግቶ በመገለጥ የሚታወቁ ነገሮች ተቀባይነት ያጣሉ:: በመሆኑም የአመክንዮ በመገለጥ ላይ መሠልጠኑ ለመገለጥ ተቀባይነት ደንቃራ የሚሆንበት ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል:: ለምሳሌ:- የተአምራት (የልዕለ ተፈጥሮአዊነት) ምስጢር በመገለጥ እንጂ በአመክንዮ ብቻ የሚፈታ አይደለም:: እንዲያው በደፈና ግን አመክንዮ በመገለጥ ላይ ይሠልጥን ከተባለ ልዕለ ተፈጥሮአዊነት ትርጉም የለሽ መሆን አለበት::

## መ. መገለጥ በአመክንዮ ላይ

መገለጥ በአመክንዮ ላይ የሚለው በጠርጡሊያኖስና በቫንቲል የተወከለው አቋም የመገለጥን የበላይነት የሚያጉላ ነው:: በርግጥ ከሥነ ኑባሬ ሥርዐት (Ontological order) አኳያ መገለጥ አመክንዮን መቅደሙ ልክ ነው:: የሆነ ሆኖ ግን መገለጥ በአመክንዮ ላይ ሲሠለጥን፣ በሁሉ ሁኔታ ውስጥ እንዳልሆነ ግልጽ ቢሆን ጠቃሚ ይሆናል:: ምክንያቱም አመክንዮ መገለጥን ሳይቃረን ሊገልጣቸው የሚችላቸው እውነቶች ስላሉ ነው:: ለምሳሌ:- በአጠቃላይ መገለጥ (General revelation) ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖር ሊገምቱ ይችላሉ:: ይህም የሚሆነው አመክንዮን በመጠቀም በሚያደርጉት በፈጣሪ መኖር ባላቸው መቅድመ ልባዌ (ቅድመ ግንዛቤ) ነው:: ይህም በሮሜ ምዕራፍ አንድ ላይ በሐዋሪያው ጳውሎስ በግልጽ ተቀምጧል::

"… እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፣ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና:: የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና… " መዝሙረኛው ተመሳሳይ ነገር ነው የተናገረው:- " ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል::" መዝሙር 18/19/፡1-2::



እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩ፣ የአራቱም አመለካከቶች የጋራ የሆነ አካሄድ በሁለት መንገድ ሊፈረጅ ይችላል:: አንደኛው ጽንፈኝነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ሚዛናዊነትን ማጉደል ነው:: ጽንፈኝነት፣ መገለጥ ብቻ በማለት አመክንዮን ማግለልን እና አመክንዮ ብቻ በማለት መገለጥን ማግለልን ያመለክታል:: ሚዛናዊነትን ማጉደል ደግሞ፣ አመክንዮ በመገለጥ ላይ በማለት እና መገለጥ በአመክንዮ ላይ በማለት አመክንዮና መገለጥ ያላቸውን ጥምረት ግልጽና አጥጋቢ በሆነ መንገድ አለማሳየት ነው:: ስለዚህ አራቱም አመለካከቶች እውነትነት ቢኖራቸውም የአመክንዮንና የእምነት ዝምድና ለብቻቸው በመቆም ሊያሳዩ የማይችሉ ናቸው:: በሌላ አገላለጽ ከላይ የተቀመጡ የአራቱም አመለካከቶች አጥጋቢ አለመሆን ሙሉ እውነት ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸው ነው:: ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት መገለጥንና አመክንዮን በማፋታት ከማስቀመጣቸው የተነሳ ነው::

# ምዕራፍ አራት

## <u>የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና</u>

የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና ጥናት የቅርብ ጊዜ ክሥተት አይደለም:: ስለዚህ ጉዳይ ጋይዝለር የተባለ ታላቅ ትምህርተ ዘለቅ (Scholar) እንደተናገረ «የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና ለሚያስብ አማኝ ትልቅ ጠቀሜታ አለው:: እነኚህን ሁለቱንም ነገሮች ለማጣመር የሚደረግ ጥረት የተጀመረው ከጥንት ዐቃቤ እምነቶች (Apologists) ጊዜ አንሥቶ ነው:: ለዚህ ዮስጦስ ሰማዕት፣ ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያና ጠርጡሊያኖስ በየፊናቸው ታግለዋል:: አውግስጢኖስ የመጀመሪያውን የማጣመር ጥረት አድርጉአል:: ነገር ግን ሰፋ ያለ የማጣመር ሥራ የተሠራው በመካከለኛው (Medieval) ክፍል ዘመን መጨረሻ ክርስቲያን ምሁራን በቶማስ አኪውነስ ሥራ ላይ ትኩረት ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ነው»[72] ዛሬም በተለያዩ ክፍለ ዘመናት ውስጥ የተለያዩ ሰዎች እይታቸውን ያንፀባረቁባቸው የአመክንዮና የእምነት ዝምድና ጥምረታቸው ተጠናቆ አነጋጋሪነታቸው የተፈጸመ ጉዳይ አይደሉም:: ከላይ የተቀመጡት አመለካከቶች



እንደ ተመለከትናቸው ሁሉ የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና መቋጫዎች አይደሉም:: ምክንያቱም የዚህ ሥራ ዋና ዐላማ የሁለቱንም ጥምረት ማሳየት በመሆኑ ነው:: ለእምነትና ለአመክንዮ ጥምረት ይረዳን ዘንድ ሁለት ጽንፎችን ማስወገድ የሚረዳን መስሎ ይታየኛል:- አንደኛው አመክንዮአዊነት (Rationalism) ነው:: ይህም ዕውቀት የሚገኘው በስሜት ሕዋሳት አማካይነት ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ከሐሳብ መመሪያዎች ወይም ከአመክንዮ ብቻ ነው ብሎ ማመን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እምነታዊነት (Fideism) ነው:: ይህም ሃይማኖታዊ እምነቶች ለአመክንዮአዊ ግምገማ የተጋለጡ ሊሆኑ አይችሉም::»[73] የሚሉ ናቸው::

እነኚህን ጽንፎች ማስወገድ፣ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው:: አሜሪካዊው ክርስቲያን ፈላስፋ ስቴፈን ኢቫንስ እንዳስቀመጠው፣ «አንድ ሰው በእምነትና በአመክንዮ ላይ ያለው አመለካከት፣ ፍልስፍናና ሃይማኖት አንዱ ለሌላኛው ጠላት፣ ሳይገናኙ በሰላም አብረው መኖራቸውን ወይም የሚተባበሩ እንደ ሆኑ አድርጎ እንዲወስን ሊያደርግ ይችላል::»[74] ይህም ብቻ ሳይሆን፣ «የእምነትና የአመክንዮ ዝምድና ችግር እንደ ኢቫንስ እምነት . . . በፍልስፍና ሃይማኖት እና በነገረ መለኮት ውስጥ ማዕከላዊ ጥያቄ ነው::»[75]

አመክንዮና እምነት ከተነጣጠሉ ከሚፈጠሩት ችግሮች አንዱ፣ ለየብቻቸው መጓዝ የማይችሉ መሆናቸው ነው። በሌላ አነጋገር አመክንዮ ለእምነት እምነትም ለአመክንዮ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። አንዱ ያለ ሌላኛው ትርጉም ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል። ይህም ሆኖ ግን እምነትም ሆነ አመክንዮ አንዱ በሌላው ላይ አላስፈላጊ በሆነ መንገድ መሠልጠን የለበትም። ሁለቱ ክርስቲያን ፈላስፎች ክሬፍትና ታሲሊ እንዳሉት፣ «አመክንዮ የእምነትን፣ የተስፋንና የፍቅርን ቀዳሚነት መጋፋት እንዳለበት አናምንም።»[76] በአግባቡ ከተጠቀምንበት አመክንዮም ሆነ እምነት ጠቀሜታቸው የጐላ ነው። ለምሳሌ:- የሥላሴ አስተምህሮ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ነገሮች መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል። አመክንዮን በመጠቀም እግዚአብሔር በባሕሪዩ አንድ መሆኑንና ያን የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ የሆኑ ሦስት አካላት አብ፣ ወልድና፣ መንፈስ ቅዱስ እንዳሉ ከሐሳብ ግጭት ነጻ በሆነ መንገድ ማሳየት ይቻላል። ነገር ግን እግዚአብሔር አንድ እንጂ ሦስት አለመሆኑን በአመክንዮ ማረጋገጥ ደግሞ የሚቻል አይሆንም። እዚህ ቦታ አመክንዮ ከእምነት ጋር ሳይቃረን ስፍራውን ለእምነት ይለቃል ማለት ነው። ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል:- የክርስቶስ ውልደት፣ የክርስቶስ ሁለት ባሕርያት (መለኮትና ትስብዕት



ወይም ሰብአዊ) በአንድ አካል መኖራቸው፣ ታምራታዊ አሠራሮችና ሌሎችም ይገኙበታል። ሁሉም ነገር በአመክንዮ እንደማይፈታ ሁሉ በእምነትም አይፈታም። «አመክንዮን በእምነት ላይ መጨመር ዕድገት ነው ነገር ግን ከእምነት በፊት አመክንዮ (ምክንያት) መጠየቅ ግን አይደለም።»[77] ይህ የሚያስረዳን «እምነትና አመክንዮ ባላንጣዎች አለመሆናቸውን ነው። ነገር ግን በኢምክኑአዊ ጥርጣሬ፣ ፍላጐት፣ ፕሮፓጋንዳ፣ ፍርሃት፣ ስንፍና፣ ሐሳብና ተፋልሶ ላይ በኅብረት የሚዘምቱ ናቸው።»[78]

እምነትና አመክንዮ ተስማምተው ሲሠሩ በሁለቱም ጥምረት የማይስማማው ሰው ነው። ይህም የሚሆነው ከየሰው ርዕዮተ ዓለም፣ ንጽሮተ ዓለምና የሃይማኖት ታሪካዊ ዳራ ልዩነት የተነሣ ነው። ይሁን እንጂ የእምነትና የአመክንዮን ዝምድና ከእግዚአብሔርና ከሰው ማንነት አኳያ ብናየው የተሻለ ነው። እግዚአብሔር በማንነቱ (በዕውቀቱ፣ በችሎታውና በሌሎች ባሕርያቱ) ኢ-ውሱን ነው። ሰው ደግሞ ውሱን ነው። በሁሉም አቅጣጫ ውሱን የሆነው የሰው ልጅ ስለ ራሱ፣ ስለ ፍጥረት ስለሌሎች ሰዎች፣ ስለ እውነታ (Reality) የሚያውቃቸው ነገሮች የሚደገፉት በአመክንዮው

አስቦ በሚደርስባቸው የማሰብ ውጤቶች አሊያም የቱንም ያህል ቢጥር ከአእምሮው ችሎታ የሚያልፉ ነገሮችን በእግዚአብሔር ኢውሱኑነትና ሉዓላዊነት በማመን በእምነት መቀበል በመቻሉ ላይ ነው:: ነገሮችን ለመረዳት በአመክንዮ ብቻ ከተደገፍን እምነት በአስተሳሰብ ሥርዐታችን ውስጥ ስፍራ አይኖረውም ማለት ነው:: ይህም ከአመክንዮ ችሎታ የሚያልፍ ማንኛውም ነገር ትርጉም ስለሌለው እምነት መፍትሔ ሊሆን አይችልም:: ለምሳሌ:- ሣራ በዘጠና ዓመት መውለዷ በአመክንዮ መንገድ ብቻ ሊፈታ አይችልም:: ይህን ለመቀበል ማመን አማራጭ የሌለው መንገድ ነው:: ይህ ደግሞ እምነትን ይጠይቃል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በችሎታው ያደረገው ከኛ አእምሮ መረዳት የሚያልፍ ነገር በመሆኑ ነው:: ይህ ሲባል ግን በሌላ ጐኑ ነገሮችን ለመረዳት ሁሌ እምነት ያስፈልገናል ማለት አይደለም:: ለምሳሌ:- 2+1=3 መሆኑን ለማወቅ እምነት አያስፈልገን ይሆናል:: ምክንያቱም 2+1=3 መሆኑ በራሱ ግልጽ በመሆኑ ነው:: ሌላ ምሳሌ ልስጥ:: አማኝ ያልሆነ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጋጫል ብሎ ተአማኒነቱን አልቀበልም ቢል፤ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደማይጋጩ በእምነት እንዲቀበል



መናገር ሳይሆን፤ መፍትሔው አመክንዮአዊ መንገድ በመጠቀም ቅዱሳት መጻሕፍት እርስ በርስ እንደማይጋጩ ለማሳመን መጣርና ለዚህም ማረጋገጫ በመስጠት እውነትን ማሳየት ነው ግራ ለተጋባው ሰው መፍትሔ ሊሆንለት የሚችለው:: ስለዚህም የአመክንዮና የእምነት ዝምድና መታየት የሚኖርበት አንዱ ለሌላው ከሚያመጣው ዕገዛ አንጻር ነው::

ፒተርና ታሲሊ የሚባሉ ሁለት ክርስቲያን ፈላስፎች በጋራ በጻፉት መጽሐፋቸው እንደተናገሩት «መኪና ወደ ባሕር አጠገብ ሊያመጣህ እንደሚችል ሁሉ ሙግቶች( Arguments) ወደ እምነት ሊያመጡህ ይችላሉ:: መኪና ሊዋኝ አይችልም:: ባሕር ውስጥ በመዝለል ያን ማድረግ ያለብህ አንተ ነህ:: ሆኖም ግን በብዙ ርቀት ላይ ሆነህ ወደ ባሕር መዝለል አትችልም:: በመጀመሪያ በእምነት ወደ ባሕሩ የምትዘልበትን ቦታ እንዲያደርስህ መኪና ያስፈልግሃል:: እምነት መዝለል ነው:: ነገር ግን የሚዘለለው በብርሃን እንጂ በጨለማ ውስጥ አይደለም::»[79] የብሌዝ ፓስካል ሀሳብ ደግሞ የበለጠውን በጠነከረ መንገድ የአመክንዮንና የእምነትን ትስስር አመላካች ነው ፓስካል ለምሳሌ ሐሳቡን ሲሰነዝር “በመጀመሪያ

ደረጃ በአመክንዮ መታመን ራሱ በአመክንዮአዊ መንገድ የሚረጋገጥ ነገር ሳይሆን፤ በእምነት የሚወሰድ ርምጃ ነው»[80] ይላል::

በእኔ አመለካከት እምነትንና አመክንዮን በማፋታትና በማጣመር ስለ ነገሮች የሚኖረን ግንዛቤ በእኩል ደረጃ ሚዛኑን የጠበቀ አይሆንም:: ነገሮችን ለአመክንዮ ብቻ መስጠት የዐቅማችንን ልክ እንዳናውቀው ያደርገናል:: ይህም በትዕቢት እንድንሞላ ያደርገናል:: ምክንያቱም ከአመክንዮ ጋር ሳይቃረን አመክንዮን ዐልፎ የሚሄድ እውነት አለና:: እምነት ብቻም ካልን መጠቀም እስከምንችለው ድረስ አእምሮአችንን እንዳንጠቀም የስንፍና እና የጥራዝ ነጠቅ ዕውቀት ባለቤቶች ያደርገናል:: አመክንዮንና እምነትን አጣምረን ከያዝን ብቻ ጥሩ ተጠቃሚዎች እንሆናለን:: አመክንዮና እምነት ባላቸው ግንኙነት እምነት የበላይ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም አመክንዮ ከተጠቃሚው ውሱንነት የተነሣ ውሱን አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ነው:: እምነት ግን ኢ-ውሱን በሆነው አምላክ ላይ የሚደረግ አለኝታ በመሆኑ፤ አመክንዮን ባይጻረርም የበላይነት ይኖረዋል:: ይህ ማለት አመክንዮና እምነት አብረው ሲጓዙ እንደ ዊሊያም ክሬግ አባባል «መንፈስ ቅዱስ ስለ መሠረታዊ የክርስቲያን እምነት እውነት በሚሰጠው



ምስክርነት በሙግትና በመረጃ ላይ በተደገፈው እምነት መካከል ግጭት ቢፈጠር ሥፍራውን መልቀቅ ያለበት የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ለሙግት ሳይሆን፤ ሙግትና መረጃ የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ማስቀደም ይኖርባቸዋል::»[81] በክርስትና እምነት ውስጥ የአመክንዮ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ ቢገባም፤ የእምነት የበላይነት ደግሞ ለድርድር የሚቀርብ አይሆንም::

እንግዲህ እምነትና አመክንዮ መጣመራቸው ስለ ነገሮች አጥጋቢ ዕውቀት ኖሮን ተጠቃሚዎች እንድንሆን ያደርገናል:: ከዚህ ባሻገር ለእኛ ለክርስቲያኖች እምነት እጅጉኑ ጠቃሚ ነው:: «የእምነትና የአመክንዮ ጋብቻ በዐቃቤ እምነት (Apologetics) ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆነ ጥያቄ ነው:: እምነትና አመክንዮ የተጋቡ ወዳጆች መሆናቸው ቀርቶ የተፋቱ ከሆኑ ወይም ደግሞ እንደ ድመቶችና ወፎች የማይስማሙ ከሆኑ እምነትን መከላከል አዳጋች ነው:: እምነትን መከላከል አመክንዮን ከእምነት ጋር ለማገናኘት የሚደረግ ጥረት ነው:: በሌላ አገላለጽ እምነትን በአመክንዮ መሣሪያ እንደ መጠበቅ ነው::»[82]

# ምዕራፍ አምስት

## የእምነትና የአመክንዮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች

የእምነትና የአመክንዮ ጥምረት ፋይዳ ሊታይ የሚገባው በተለያዩ ጊዜያት ተነሥተው ከነበሩ የታሪክ ክስተቶች አኳያ ብቻ ሳይሆን፣ መሠረታዊ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ጭምር ነው።

ሀ. እምነት፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእምነት መሠረት እግዚአብሔር ነው። እምነት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ የሚያበቃው የመግቢያ በር ነው። ይሁን እንጂ በባሕርይው እምነት ጭፍን አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ግልጽ አድርጎ እንዳስቀመጠው እምነት አማኙን ወደ ረጂውና ወደ በላዩ አካል የሚያስጠጋ ኃይል ነው። የዚህን ሙሉ ገጽታ ለመረዳት የብሉይና አዲስ ኪዳንን የእምነት እይታ ማጤን ጠቃሚ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት የገለጹት ከጠላቶቻቸው እጅ ለመዳን፣ ከተፈጥሮ አደጋዎች ለማምለጥ፣ ምሕረት ለማግኘት፣ ለተስፋ ቃል መፈጸም ለዕለት ተዕለት



ኑሮ ፍላጎቶችና ሌሎችም ነገሮች ነበር። ከዚህ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት አቅጣጫ የለሽ እንዳልሆነ እንረዳለን። ሰዎች ሲያምኑ የእምነታቸውን ባለቤት ያውቃሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን የእምነታቸው ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር የሰጣቸውን እውነት በእምነት ተቀብለው ዘወትር ሊኖሩበት የሚለማመዱት ሕይወት ነው። ጄ አይ ፓከር የተባለ ስመ ጥር የነገር መለኮት ምሁር በበኩሉ ስለ አዲስ ኪዳን እምነት ምንነት ጠቃሚ አሳብ ሰንዝሯል። «እምነት በተቀበሉት እውነት መኖር ነው። በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ የተመሠረተ እምነት ለእግዚብሔር ክብር እየሠራ ለእግዚአብሔር ጸጋ ምስጋና ይሰጣል።»[83]

እምነት ባዶ ነገር ማመን ሳይሆን፣ የሚያምነውን ሰው ንቁ የማወቅ ተሳትፎ የሚጠይቅ ልምምድ ነው። በሌላ አባባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በድንግዝግዝ ውስጥ መመላለስ አይደለም። ይህ እምነት ውሳኔን የሚጠይቅ በመሆኑ ከዕውቀት ጋር የተገናኘ ነው። በተወሰነ ደረጃ ሰው ለውሳኔ የሚያበቃውን ያህል ዕውቀት ስለሚያምነው ነገር መጨበጥ ይኖርበታል። ለምሳሌ የአብርሃምን ሕይወት ስናይ እግዚአብሔር ከአገሩ እንዲወጣ

ሲጠይቀው እግዚአብሔር እንደ ጠራው በማወቅ አምኖ ቃሉን ለመታዘዝ ወስኖ ተነሣ:: እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን እንደሚፈጽማቸው አመነ:: በተከታታይ አብርሃም እግዚአብሔር እንደሚመራውና ለሕይወቱ አስፈላጊ ነገር እንደሚሰጠው አመነ (ዘፍ. 12:15-14):: /ምዕራፍ 12፤15፤17፣18 ወዘተ/ አብርሃም በሕይወቱ የታዩ ድካሞች ቢኖሩም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ለማመን ቢያንስ የተስፋዎቹ ምንጭና ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ማወቅና ማመን ነበረበት::

እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ «በእግዚአብሔር መታመን ነው፤ ይህ አለኝታ ደግሞ እግዚአብሔር የሚለው ነገር እንዲታመን መሠረት ጣይ ነው»[84] አብርሃም ለቤተሰቡ ከተገባለት የተስፋ ቃል በላይ፤ እግዚአብሔር አንድ ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግለት ሲጠይቀው የሰጠው ምላሽ በራሱ ትልቅ እምነት የሚጠይቅ ጉዳይ ነበር (ዘፍ. 22):: ይሁን እንጂ ከአብርሃም የእምነት ርምጃዎች አሜሪካን ባለው የሚሽጋን ግዛት ውስጥ በግራንድ ቫሊ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚያስተምር ዲዊ ሆትንጋ እንዳስተዋለው ሦስት ነገሮችን እናያለን:- እነዚህም "አለኝታ፣ እምነት እና መታዘዝ»[85] ናቸው::



የእነኚህ የሦስቱም ነገሮች ጥምረት ውጤት ነው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት መገለጫ የሚሆነው:: እምነት የሚታመኑ እውነቶችን ያመለክታል (ይሁዳ 3፤ ሮሜ 1፣5፤ገላ. 1፣23፤ገላ.1፣23፤1ኛጢሞ.4፣ 1-6)[86] ክርስቶስ ተአምራት ለመሥራት ከሚደረግ መታመን ጋር እምነትን አገናኝቶታል (ማቴ. 17፣20፤ 1ኛቆሮ. 12፣9፤ 13፣2)[87] መልእክቶች እምነትን ከማወቅ፣ ከማመን እና ከመታዘዝ ጋር የተ ገናኘ ጉዳይ መሆኑን ያሳያሉ (ቲቶ. 1፣1፤ 2ኛተሰ. 2፣13፤ 1ኛጴጥ. 1፣22 ወዘተ)[88]

እንደ ጂ. አይ. ፓከር እይታ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ሊጠቃለል ይችላል::

1. ስለ እግዚአብሔር ልክ የሆነ እምነት ያካትታል::

2. እምነት በመለኮት ምስክርነት ላይ የተመሠረተ ነው (1ኛዮሐ. 3፣2፤ 5፣18-20፤ ዮሐ. 3፣11፣ ሐዋ. 10፣39-43)::

3. እምነት መለኮታዊ ስጦታ ነው (ኤፌ. 4፣18፤ 2ኛ ቆሮ. 4፣4፤ ዮሐ. 3፣3፤ 1ኛቆሮ. 2፣14፤ ዮሐ. 6፣44፤ 1ኛዮሐ. 2፣20:27፤ ኤፌ.2፣8፤ ፊል. 1፣29)[89]

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ባዶ አይደለም:: እግዚአብሔርን ማወቅ፣ መታዘዝና መታመን ይጠይቃል:: እግዚአብሔር የሚሠራቸው ሥራዎች ምስጢራዊ በሚሆኑበት ወቅት እንኳ ቢሆን፣ በእርሱ በመታመን የአድራጊውን ችሎታ ከግምት በማስገባት፣ ቅድሚያ ለእግዚአብሔር የሚሰጥበት ልምምድ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በሠሪው ብርታትና ማንነት ላይ ትኩረት ማድረግን እንጂ የአሠራሩን ምስጢር የማወቅ ግዴታ አይጭንብንም:: አብርሃም «የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" ሲል ሁሉን ነገር ለሁሉ ቻይ አምላክ አስ ረከበ እንጂ ምርምር ውስጥ አልገባም» (ዘፍ. 22)::

እምነት ምንድን ነው? የሐሳብ ፈረስ መጋለብ፣ ወይም በጨለማ ውስጥ መዝለል አይደለም:: ለአብርሃም እምነት እግዚአብሔር ከገለጠለት ነገር መጀመር ነው:: እግዚአብሔር ቃል የገባውን ተስፋ ሲፈጽም ኃይል እንዳለው ሙሉ በሙሉ ማመን ነበር (ሮሜ 4፣21)::»[90] ስለሆነም «በእግዚአብሔር ማመን እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ እርሱንም ማወቅ በእርሱ ማመን ነው»[91]



## ሰ. አመክንዮ

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በአምሳሉ መፍጠሩ ከሚታወቅባቸው መንገዶች አንዱ፣ ሰው ማሰብ መቻሉ ነው:: በሌላ በኩል ስናይ ግን ወንበር ማሰብ አይችልም:: እንስሳ፣ እንስሳ መሆኑን ወይም ስለ ራሱ ማንነት ማሰብ አይችልም:: ሰው ግን ስለ ሌሎች ነገሮች ብቻም ሳይሆን ስለ ራሱ ማንነት ማሰብ የሚችል ፍጡር ነው:: ሰው ከየት መጣሁኝ ብሎ ጥያቄ ያነሳል፣ መጨረሻዬ የት ነው በማለትም ይጠይቃል:: በጥቅሉ ሰው ጠያቂ ነው::

ከዚህ የተነሣ ነው እግዚአብሔር ሰውን ለሚያደርጋቸው ነገሮች ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት በቃሉ የደነገገው:: አመክንዮ የአእምሮ ሥራ እንደ መሆኑ አእምሮአችን መታደስ እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው::" (ሮሜ12፣1):: በተጨማሪም ደግሞ እግዚአብሔርን በአእምሮአችን መውደድ

እንዳለብን የኢየሱስ ትምህርት ያሳየናል "ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍ ጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ" (ማቴ.22፤37)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ ከሕዝቡ ጋር ሊወቃቀስ ፈልጎ «ኑ እንዋቀስ» በማለት ሕዝበ እሥራኤልን ለድርድር ሲጋብዝ እናነባለን (ኢሳ.1፤18)። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት የዚሁ የአመክንዮ ጠቀሜታ ነጸብራቅ ነው። ኢየሱስ መለኮታዊ ኃይሉን ተጠቅሞ ሰው ትምህርቱን በጭፍን ሳይረዳ እንዲቀበል ማንንም ሲያስፈራራ አናይም።

አራቱንም ወንጌላት (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ )ስንመለከት ኢየሱስ ከፈሪሳውያን፣ ከሰዱቃውያን፣ ከጸሓፍትና ከሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር በነበረው ግንኙነት፣ ተቃዋሚዎቹንም ሆነ ተከታዮቹን አመክንዮ በመጠቀም ሲያስተ ምራቸውና ሲሞግታቸው ከወንጌላቱ እንማራለን። ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት እንኳ ሲናገር፣ ከሥራው በመነሣት መረጃ ሲሰጥ ይስተዋላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አእምሮን መጠቀም ተገቢ እንጂ የማያስፈልግ ሆኖ አልተቀመጠም። ይህን ሃሳብ በተ መለከተ በጣም ጥሩ ሥራ ዴንቨር ሴሚነሪ ውስጥ



የፍልስፍና ትምህርት መምህር በሆነው በዳግላስ ግሩታየስ ተሠርቶአል[92]። ከዚህ በመነሳት ለመረዳት እንደምንችለው ለኛ ለክርስቲያኖች አመክንዮ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ትእዛዝ ነው[93]። በሌላ አገላ ለጽ «ከቅድስና ቀጥሎ ለክርስቲያኖች ምርጥ ነገር ቢኖር ሥነ አመክንዮ ነው»[94]፤ ንጹሕ ኑሮና ልክ የሆነ አስተሳሰብ ኃይለኛ ውኅደት ይፈጥራሉ። በአጭሩ በውጭ ሕይወታችንን በውስጥ አስተሳሰባችንን ማጽዳት አለብን »[95]።

እግዚአብሔርን ለማምለክ አእምሮአችን «መታደሱ» አስፈላጊ እንደሆነ አጽንአት መስጠቱ፣ የእግዚአብሔር ቃል ለአመክንዮ የሚሰጠውን ስፍራ ያመለክታል። እግዚአብሔር የፈጠረው ዓለም ራሱ ሥርዐት ያለው እንደ መሆኑ ይህን ዓለም ለመረዳት ደግሞ አመክንዮ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። አመክንዮ ከሰው ኃጢአት የተነሣ የተጐዳ መሆኑ ግልጽ ነው "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፣ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የማያመካኙት አጡ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለ

ውም ልባቸው ጨለመ:: ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ የማይጠፋው ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ::" (ሮሜ 1፣ 20-23):: ሐዋርያው ጳውሎስ እንደገና ሲናገር «ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋልና፤ የእግዚብአብሔርም ክብር ጉድሎአቸዋል» (ሮሜ3፣23) ይላል:: በአእምሮአችን መታደስ ብንለወጥ ደግሞ አመክንዮአችን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ሊመለስ ይችላል:: ይህ መጽሐፍ ቅዱስም የሚያስተምረን እውነት ነው "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው:: የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ::" (ሮሜ.12፣1-2):: የአእምሮ መታደስ ደግሞ ለአእምሮ ከማይመች አመክንዮአዊ አስተሳሰብ የሚመልሰን ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሃሳብ በሌላ መልዕክቱ ሲያጠናክረው:- "እንደ ክርስቶስ ትምህርት



ሳይሆን እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ::" (ቈላስይስ2፣8፣1ቆሮ.1-2):: አሜሪካዊው እውቅ ክርስቲያን ፈላስፋ ጄ.ፒ ሞርላንድ እንዳለው "የውድቀት አስተምህሮ (Doctrine of fall) አመክንዮ እንደማይጠቅም አያሳይም::[96] ከዚህ ጋር በተያያዘ መረዳት ያለብን ሌላው ነገር «አመክንዮ አንድን ሰው ወደ ክርስቶስ ባያመጣውም አመክንዮን በመጠቀም ሰውን ማሳመን ወይም ከሰው ጋር ውይይት ውስጥ መግባት የለብንም ወደሚል ድምዳሜ ሊመራን እንደማይችል ነው::»[97]

# ምዕራፍ ስድስት

## በእምነትና በአመክንዮ ዙሪያ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች

በዚህ ስፍራ አመክንዮንና እምነትን በሚመለከት በተደጋጋሚ ከሚነሡ ነጥቦች መካከል፣ ከአገራችን ዐውድ ጋር ሲሄዱ የሚችሉትን አራት የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ለሦስተኛ ጊዜ ከታተመው መልስ ይኖ ረው ይሆን?” መጽሐፌ ውስጥ ከገጽ 103-106[98] ካለው ክፍል በስፋት ልጥቀስ:-

### 1. አመክንዮን መጠቀም እንደ መንፈሳዊ ድካም መቍጠር

ብዙ ሰዎች « ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል» (2ኛ ቆሮ.3፣6) የሚለውን የጳውሎስን አሳብ በተሳሳተ መልኩ በመረዳት ለዕ ውቀት የሚሰጡት ስፍራ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: መንፈሳዊነት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በቅጡ ያለመረዳት፣ መንፈሳዊ ያልሆነውን ነገር እንደ መንፈሳዊ ነገር ቈጥረን አምነን እንድንቀበለው ሊያደርገን ይችላል:: ለምሳሌ በቀላሉ እንኳ ብናይ፣



በዘመናችን አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊነት ማለት መጸለይ፣ መጾም፣ መስበክ፣ በልሳን መናገርና ሌሎችንም የጸጋ ስጦታዎች ለመተግበር መጣር እንደ ሆነ ያምናሉ፤ ይህንንም ይናገራሉ:: ይህ አሳብ እውነትነት ቢኖረውም በተቃራኒ ጐኑ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅና መመራመር ለመንፈሳዊ ሕይወት ድርቀትና መቀጨጭ በር ከፋች እንደ ሆነ አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ:: በመ ጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ዕውቀት ማጣት ለመንፈሳዊ ሕይወት ጸር እንደ ሆነ፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፣ «መጻሕፍትን አታውቁምና ትስታላችሁ» እያለ ሲዘልፋቸው እናያለን (ማቴዎስ 22፣29):: ሐዋርያው ጳውሎስ በበኩሉ በበርካታ መልእክቶቹ ውስጥ ለተደራስያኑ የሐሰት ትምህርትን ለመከላከል በእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ተክነው አስተሳሰባቸው አመክንዮአዊ መሆን እንዳለበት አበክሮ ተናግሮአል:: ከዚያም ዐልፎ ጳውሎስ ራሱ ለዚህ ነገር ዐይነተኛ ምሳሌ ነው (የሐዋ. 14፣15-17፤ 17፣2-4፤ 18፣4፤ 19፣8-9):: ታዲያ እዚህ ላይ ጳውሎስ እያሳየን ያለው ዕውቀት በሥርዐት ካልተያዘ የሚያመጣውን አደጋ

ነው? ወይስ ደግሞ ዕውቀት ከቶውኑ እንደማያስፈልገን ነው? ክርስቲያኖች በአስተሳሰባቸው አመክንዮአዊ ከሆኑ፣ በቀላሉ ለሚመጣው ለማንኛ ውም ዐይነት እምነታቸውን ሊያናጋ ለሚችል የሐሰት ትምህርት ውዥንብር ጥቃት የተጋለጡ አይሆኑም:: እንዲህ ስንል ግን፣ አመክንዮአዊነት በራሱ የሰው ሕይወት ጠባቂ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: ሰውን የሚያጸናው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ዕውቀት በጸሎትና በጾም ሊተካ እንደማይችል ሁሉ፣ ጸሎትም በራሱ ያለ ዕውቀት ውጤት አያመጣም:: ለዚህ ነው የእግዚአብሔር ቃል «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም አሳብ ውደድ» የሚለው (ማቴ.22፣37):: ይህ ቃል ሁለቱንም ማለትም የዕውቀትንም የመታዘዝንም ነገር በሚገባ በውስጡ የያዘ ትእዛዝ ነው:: ለዚህ ነው ሰው በዕውቀት ሲካን፣ የበለጠውን ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገትና ብስለት በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል መታመን የሚ ኖርበት:: ይህ እውነት ሆኖ ሳለ ግን እግዚአብሔርን በማወቅ ላይ ያልተመ ሰረተና ለእግዚአብሔር የማይገዛ እውቀት ለመንፈሳዊ ሕይወት አደጋ ሊያስከትል የሚችል



መሆኑን መረዳት አለብን:: አመክንዮ ጠቃሚ ቢሆንም፣ አመክንዮ በእግዚአብሔር እውነት የማይገራ ከሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ብዙ ነው:: አመክንዮ የእምነት አገልጋይ እንጂ እምነት የአመክንዮ አገልጋይ ሊሆን አይገባም:: ስለዚህ የአመክንዮን ጠቀሜታ ብንቀበልም ያለ አግባብ በሥራ ላይ ካዋልነው የእምነታችንን መሠረት ሊያናጋ ይችላል:: በጥቅሉ ግን አመክንዮ የመንፈሳዊ ሕይወት ጠላት አይደለም::

ይህ አሳብ ዕውቁ ክርስቲያን ፈላስፋ ጄ.ፒ ሞርላንድ "አምላክህን በፍጹም አሳብህ ውደድ" በሚል እ.ኤ.አ በ1997 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ በአስደናቂ ሁኔታ በስፋት ይገኛል::

## 2. አመክንዮ በመንፈስ ቅዱስ ያለመደገፍ/ ያለመታመን/ ውጤት ነው ብሎ ማሰብ

አንድ ሰው የሚያስብና ነገሮችን የሚመራመር ከሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ ያለመደገፉን ያሳያል፣ ብሎ ማመን ልክ አይደለም:: ይህ የተሳሳተ፣ ከእውነት ፈቀቅ ያለ አመለካከት ሊመነጭ የሚችለው መንፈስ

ቅዱስ ሲሠራ ሰውን እንደ አሻንጉሊት እንዳሻው ይጠቀምበታል ብሎ ከማመን የሚመነጭ ነው:: በጥቅሉ አንድን ነገር ማየትና ማመዛዘን እንደአላስፈላጊ ነገር መቍጠሩ ከስንፍና ምንጭ የሚቀዳ ውሃ ነው::ወንጌላት እንደሚነግሩን መንፈስ ቅዱስ አስተማሪያችን ነው:: "ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል::" (ዮሐንስ 14፤25-26):: እኛ ደግሞ ተማሪዎቹ ነን:: የምንማረው ግን ያለ ምንም ድርሻ መወጣት ሳይሆን የምንማረው ትምህርት ከመንፈስ ቅዱስ ይሁን ወይም ከሌላ የመጣ መሆኑን ለመለየት፣ ረቀቅ ያለ የአስተሳሰብ ችሎታ ያለን ባለአእምሮዎች መሆን አስፈላጊ እንጂ፣ የምርጫ ጉዳይ አይሆንም:: ይህ ለሁሉም ሰው ይሆናል ማለቴ ባይሆንም፣ የእግዚአብሔር ቃል የሚያዝዘን ግን ይህንኑ በተቻለ መጠን እንድናደርግ ነው:: በበዓለ ኀምሳ ቀን የሐዋርያው ጴጥሮስ ስብከት አመክንዮአዊ መሆኑ መች የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አገደው? ይልቁን የንግግሩን ውጤት በአዎንታዊው ጐኑ ሥር ነቀል አደረገው እንጂ (የሐዋ. 2):: መንፈስ ቅዱስ



አእምሮአችንን ይፈልገዋል:: በዚያውም ልክ ደግሞ ሥራውን ይሠራል:: ይኸው መንፈስ ደግሞ ለብቻው አይሠራም:: ይህ ማለት ግን መንፈስ ቅዱስ በኛ ላይ ሳይደገፍ ሊሠራ አይችልም ማለት አይደለም:: በሌላ አገላለጽ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በመሆኑ የኛ በርሱ ላይ መደገፍ አማራጭ የለውም:: ሆኖም ግን መንፈስ ቅዱስ ከኛ ጋር ይሰራል:: ይህም እኛን እንደ መሣሪያ አድርጎ በመጠቀም ሥራውን ይሠራል ማለት ነው:: ከዚህ በመነሳት እኛ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተባብረን እንሰራለን ማለት ነው:: ይህም ማለት እግዚአብሔር እኛንና ያለንን ብቃት ጭምር ይፈልጋል:: ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን የምንሠራ ነን እንጂ፣ ተለያይተን የየራሳችንን ጉዳይ የምናስፈጽም አይደለንም:: ይህም ሆኖ ግን መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንደመሆኑ ያለ እኛ የፈለገውን ሥራ ሊሰራ እንደሚችል መዘንጋት የለብንም::

## 3. አመክንዮ በባሕላችን ውስጥ የሚበረታታና የሚሞገስ አይደለም::

ባህል በባህልነቱ ከታየ የሚጠላ ነገር አይደለም:: የባህል ምንነት ሊፈተሽ የሚችለው ግን፣

አንድ ባህል ምን ዐይነት ድርጊት እንዲከናወን ያበረታታል? የትኛውንስ ያወግዛል? ወደሚል ነገር ሲመጣ ብቻ ነው:: አመክንዮን በሚመለከት የአገራችን ባህል እጅን ዘርግቶ የሚቀበለው ነገር አይመስልም::

እንደ ዕድል ሆኖ ከልጅነታችን ጀምሮ በዕድሜ ጠና ያሉ ሰዎች የሚሉትና ያመኑት ነገር ልክ እንደሆነና ወጣቶችና ልጆች ምንም አያውቁም በማለት ነገሮችን በግል መረዳትና መቀበል የሚያዘልቅ አይደለም የሚል እምነት ይዘን እናድጋለን:: ለምሳሌ:- በባህላችን አንድ ትልቅ ሰው የተናገረውን ነገር መገምገምና በሚሳሳትበት ጊዜ ልክ ያለመሆኑን መግለጽ በጣም አደገኛና መደረግም የሌለበት ነውር ነው:: «እኔ ብያለሁና ይሁን» ሲባል ለምን ብሎ ምክንያት መፈለግ የዐመፅ ርምጃ ለመውሰድ እንደ መከጀል ሊቈጠር ይችላል:: በዕድሜ ከአንድ ሰው መብለጥም ሆነ ማነስ ከብስለት አኳያ የራሱ የሆነ ድርሻ ቢኖረውም፣ አመክንዮን መጻረር ግን የለበትም:: በሌላ ጐኑ ባህላችን ማንበብን፣መመራመርን ለሁለንተናዊ ዕድገት አዎንታዊ ጎስ መቀባበልን ስለማያበረታታ ወይም እነኚህ ነገሮች አጥጋቢ በሆነ መልኩ የባህላችን አካል



ባለመሆናቸው አመክንዮ ተዳፍኖአል ማለት ይቻላል:: ከዚህ የተነሣም አንድን ነገር ሰው ስላመነ ብቻ ማመን ሲተወው ደግሞ መተው የተለመደ ሆኗል::

## <u>4. ስለ እምነት ያሉን የተሳሳቱ አመለካከቶች</u>

ይህ ነጥብ ትልቅ ጥንቃቄ የሚያሻው ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: ስለ እምነት ስናስብ እምነት እጅግ በጣም ከሚያስፈልጉን ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ነገር ነው:: መንፈሳዊ ሕይወታችንን በተመለከተ፣ ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ሰዎች ባለን አመለካከት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ከእምነት ጋር የተያያዘ ነገር ነው:: ለምሳሌ አንድ ሰው እምነት አለው ተብሎ ከታመነ መንፈሳዊ ሰው ነው ይባላል:: እምነት ከሌለው ግን እንደ ደካማ ክርስቲያን ይታያል:: እኛም ብንሆን እንደዚያው እናስባለን:: ነገር ግን እምነት ምንድር ነው? ምንስ ማለት ነው? መለኪያውስ ምንድር ነው? እነኚ ህና መሰል ጥያቄዎች በሙሉ በትክክልና በሥርዐት ሊመለሱ የሚችሉት መጀመሪያ «እምነት» ምን እንደ ሆነ በቅጡ ስንረዳ ብቻ ነው::

እምነት በብዙ ሰዎች አመለካከት ያለ ምንም

መሠረት አንድ የታሰበ ነገር ዝም ብሎ ይሆናል በማለት፣ አንድ ነገር ሊሆን እንደሚችል ማመን ነው፡፡ እምነት ይህ ከሆነ ደግሞ «እምነት» ጉም ከመዝገን እንዴት ይለያል? ጉም ደግሞ መዝገን ስለማይቻል እምነትንስ ያለ መሠረት እንዴት እምነት ነው ብሎ ማመን ይቻላል? መጽሐፍ ቅዱስ እምነት አይታይም፣ አይጨበጥም፣ አይዳሰስም የሚል መልእክት እንዳለው ስለሚታሰብ እምነት እንደ ትርጉም የለሽ (Absurd) ነገር ሲወሰድ ይታያል፡፡

ያም ሆነ ይህ እምነት ምንድር ነው? ተገቢ ጥያቄ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- «ኢየሱስ ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣ» እኛ ክርስቲያኖች እናምናለን፡፡ ሆኖም ተሞክሮአዊ (Empirical Evidence) ማስረጃ ልናቀርብ አንችልም፡፡ ይህ ሊሆን የማይችለው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በዓለማት ታሪክ ውስጥ አንድ ጊዜ የሚከሠት ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስተምረን ግን፣ እውነት እንደ ሆነ እናምናለን፡፡ እዚህ ላይ ማጤን ያለብን እምነታችን በሐቅ ላይ የተመሠረተ እንጂ፣ ከአንድ ከማይታወቅ ቦታ ዘሎ የመጣ አለመሆኑን ነው፡፡ ስለ እምነት ምንነት በሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረንን ነገር ለመረዳት ደግሞ፣ መጽሐፍ ቅዱስንም ሌሎች መጻሕፍትን ማንበብ እጅግ ተገቢ ነው፡፡



## 5. አመክንዮን እንደ ሁለንተና የመውሰድ ችግር

አመክንዮን በአሉታዊ መንገድ ማየቱ በራሱ ጉዳት የሚያስከትል ቢሆንም በሌላ ጎኑ ደግሞ ያለ አመክንዮ ምንም ነገር እንደማይሆን ማሰቡም የተሳሳተ አካሄድ ነው፡፡ አመክንዮ ሁለንተናዊ ሚና ሊጫወት አይችልም፡፡ ይህ ስህተት በአብዛኛው የሚታየው የከፍተኛ ተቋማት ትምህርት ቀመስ በሆኑ ወገኖች ዘንድ ነው፡፡ ብዙ መማርና ማወቅ መልካም ነው፡፡ የመማር ውጤቱ ግን የብዙ ማወቅን ውሱንነት ጭምር የሚያስገነዝበን እንጂ ካለኛ ማን አለ የሚያስብለን ሊሆን አይገባም፡፡ የግሪኩ ፈላስፋ ሶቅራጥስ (Socrates) በአቴንስ ከተማ ውስጥ ብዙ የሚያውቅ ሰው እንደሆነ ሲወራ ሥራዬ ብሎ የተያያዘው ከተማውን በሙሉ እየዞረ ከርሱ የተሻሉ ሰዎች እንዳሉ መፈለግ ነበር፡፡ ሶቅራጥስ ብዙ እንደሚያውቅ ስለ ራሱ መመስከርም ይሁን የሌሎችንም ስለርሱ ማወቅ ምስክርነት አጥብቆ ይቃወም ነበር፡፡ በተቃራኒ መልኩ አለማወቄን አውቃለሁ የሚል አቋም ነበረው፡፡

በዚህ ስፍራ ነጥቤ ለአመክንዮ ወሰን አለውና እውቀታችን ልከኛ እንደሆነ መገንዘብ አለብን ለማለት ነው።ቢያንስ አመክንዮን ሳንቃወም እንደ ሶቅራጥስ ልከኞች መሆናችንንም መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ፈላስፋው ገደብ ያለው እውቀት እንዳለው ሲናገር መጽሐፍ ቅዱስ በሚነግረን በእግዚአብሔር መኖር ያምን ስለነበረ ሳይሆን ከነበረው በሳል ግንዛቤ አኳያ ብቻ ነበር። ከታሪክ አኳያ ሲታይ በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው አመክንዮን እንደ ሁለንተና ማየት እስከ ዛሬ ድረስ ለዘለቀው ለእምነትና ለአመክንዮ መፋታት ምክንያት ሆኗል።

እንግዲህ አንዱም እምነትና አመክንዮን በሚመለከት ከሚነሱ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ውስጥ አመክንዮን መጥላት ብቻም ሳይሆን የአመክንዮ ወዳጆች ካለርሱ ማን አለን የሚል የተዛባ አቋም መያዛቸው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ይህን አካሄድ አይደግፈውም። "...ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቡ ስላላወቀች፣ በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን



ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና። መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ። እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ፣ለአህዛብም ሞኝነት ነው፣ ለተጠሩት ግን አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው። ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታል (1ኛቆሮ.1:20-25)።

# ምዕራፍ ሰባት

## ማጠቃለያ

እምነት ከአለኝታ፣ ከማመንና ከመታዘዝ አንጻር ሊታይ ይገባል:: እምነትና አመክንዮ ሲጣመሩ ለምሉዕ የነገሮች ግንዛቤ ዕድል ይኖረናል:: እምነት ብቻ የሚል ጽንፍ መያዝ ወደ እምነታዊነት (Fideism) ይወስደናል:: «አመክንዮ ብቻ» የሚለው ጽንፍ ደግሞ ወደ አመክንዮአዊነት (Rationalism) ጽንፍ ይወስደናል:: ሚዛኑን የጠበቀ የእምነትና የአመክንዮ ግንዛቤ ከሁለቱም ትስስር አኳያ ይሆናል::

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጉልቶ የወጣው የእምነት በላይነትና የአመክንዮ አገልጋይነት ነው:: ለዚህ ደግሞ አውግስጢኖስ፣ ቶማስ አኩዊናስ፣ ማርቲን ሉተር፣ ጆን ካልቪን፣ ብሌዝ ፓስካልና ሌሎችም ሰዎች ምስክሮች ናቸው:: እምነትና አመክንዮን ሊያፋቱ የሞከሩ ሰዎች አካሄድ፣ ለብዙ ነገሮች አጥጋቢ የሆነ ገለጻ የመስጠት ዐቅም ሲያንሰው ይታያል:: በዚህ ረገድ ካንት፣ ስፒኖዛ፣ ኪርክጋርድ፣ ባርትና ሌሎችም ሰዎች ተጠቃሽ ናቸው::



የእምነትና የአመክንዮ ጥምረት አቋም ሚዛናዊነቱ ከእስከአሁኑ ውይይት ግልጽ ሊሆን የሚችል ነው:: ሲ. ኤስ ሉዊስ እንደተናገረው «... እምነት አመክንዮ አንዴውኑ የተቀበላቸውን ነገሮች የመያዝ ጥበብ ነው...»[99]

አመክንዮንና እምነትን የማፋታቱ ግንዛቤ በዳንኤል ቴይለር እንደ ተባለው «አመክንዮ በእግዚአብሔር ማመን ኢአመክንዮአዊ (Irrational) እንደ ሆነ ያሳያል ብሎ ከማሰብ የበለጠ ጥራዝ ነጠቅ የአመክንዮ አጠቃቀም የለም» ይህ ልክ አይደለም:: ማንም ሰው ቢሆን በዚህ መልክ ሙግቱን (Argument) ቢገነባ የአመክንዮ ሆነ የእምነት ምንነት አልገባውም»[100] የእምነትና የአመክንዮ ትስስር እንዲገባን ዊሊያም ክሬግ እንዳስቀመጠው ማመን ያለብን ነገር ቢኖር «ምንም እንኳ ሙግቶች እና መረጃዎች የአማኝን እምነት ለመደገፍ ጥቅም ላይ ሊውሉ ቢችሉም፣ የእምነት መሠረት ግን አይደሉም:: ለአማኝ እግዚአብሔር የክርክር ማጠቃለያ አይደለም ነገር ግን የአብርሃም፣የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ በውስጣችን የሚኖር ሕያው አምላክ ነው»[101]

እምነት እንደማያስፈልገን ማሰብ ከዐመጸኛው ባሕርያችን ሊመነጭ የሚችል አስተሳሰብ ነው:: ለእምነት ስፍራ ስንሰጥ ለእምነታችን ባለቤት የምንሰጠው የከበረ ስፍራ አለ:: በአመክንዮ ብቻ ስንደገፍ ራሳችንን፣ በራሳችንና በሌሎች ነገሮች ላይ ጭምር መሾማችን ነው:: ይህ ሲሆን ደግሞ፣ አመክንዮ የትዕቢት በር ይሆናል:: እምነት ግን የጸጋና የመለኮታዊ ኀይል መለማመጃ መንገድ ነው:: ከትዕቢት ማምለጫ መንገድ የአመክንዮ ለእምነት መገዛትና የእምነት በአመክንዮ ላይ መመሥረት ነው:: እምነት ትርጉም የለሽ ነገር እንዳይሆን፣ አመክንዮአዊ መሠረት ያስፈልገዋል:: ሆኖም ግን እምነት ከአመክንዮ የበለጠ የመለኮታዊ እውነቶች ምንነት ገላጭ ነው:: ይህም ደግሞ አመክንዮን በመሣሪያነት በመጠቀም ነው:: ስለዚህ እምነትና አመክንዮ የተጣመሩ ወይስ የተፋቱ? ለሚለው የመግቢያ ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ ሊሆን የሚችለው የተጣመሩ የሚለው ነው::



## አጠር ያለ የቁልፍ ሰዎች ማንነት መግለጫ

አውግስጢኖስ(Augustine):- ከ354-430 ዓ/ም የኖረ ዕውቅ ፈላስፋና የነገረ መለኮት ሰው ነው::

ቶማስ አኪውነስ (Thomas Aquinas):- ከ1224-1274 ዓ/ም የኖረ የመካከለኛው ዘመን ስመ ጥር ፈላስፋና የነገረ መለኮት ሰው ነው::

ማርቲን ሉተር (Martin Luther):- ከ1483-1546 ዓ/ም የኖረ የነገረ መለኮት ሰውና የ16ኛው ክፍለ ዘመን የጀርመን የፕሮቴስታንቶች ተሃድሶ እንቅስቃሴ መሪ ነው::

ጆን ካልቪን (John Calvin):- ከ1509-1564 ዓ/ም የኖረ የነገረ መለኮት ሰውና የ16ኛው ክፍለ ዘመን የጄኔቫ የተሃድሶ እንቅስቃሴ መሪ ነው::

ብሌዝ ፓስካል(Blaise Pascal) :-ከ1623-1662 ዓ/ም የኖረ ስመ ጥር ፈረንሳዊ ሳይንቲስትና አቃቤ እምነት ነው

ቤኒዲክት ስፒኖዛ (Baruch Spinoza):- ከ1632-1677 ዓ/ም የኖረ አይሁዳዊ የአመክዮ አዊነት (rationalism) ፈላስፋ ነው::

ፍሬድሪክ ሽየርማከር (Friedrich Schleiermacher):- ከ1768-1834 ዓ/ም የኖረ የፕሮቴስታንት ለዘብተኛ (Liberal) ነገረ መለኮት አራማጅ ነው።

ሶረን ኪርክጋርድ(Soren Kierkegaard):- ከ1813-1855 ዓ/ም የኖረ ዴንማርካዊ ክርስቲያን ፈላስፋና የነገረ መለኮት ሰው ነው።

ካርል ባርት:- (Karl Barth) ከ1888-1968 ዓ/ም የኖረ ጀርመናዊ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ የነገረ መለኮት ሰው ነው።

ሪዶልፍ ቡልትማን (Rudolf Bultmann):- ከ1884-1976 ዓ/ም የኖረ ጀርመናዊ የአዲስ ኪዳን ሊቅና የነገረ መለኮት ሰው ነው።

ኢማኑኤል ካንት:- (Immanuel Kant)ከ1724-1804 ዓ/ም የኖረ ስመ ጥር ጀርመናዊ ፈላስፋ ነው።

ዮስጦስ ሰማዕት(Justin Martyr):– ከ105-165 ዓ/ም የኖረ የግሪክ ተናጋሪ ታላቅ የቤተክርስቲያን አባት ነው።

ቀለሜንጦስ ዘእስክንድሪያ (Clement of Alexandria):- ከ150-220 ዓ/ም የኖረ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።

ጠርጡሊያኖስ (Turtullian):- ከ160-230 ዓ/ም የኖረ የላቲን ፀሐፊ የሆነ ታዋቂ የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።



ኮርኒሊየስ ቫንቲል (Cornelius Van Til):- ከ1896-1987 ዓ/ም የኖረ የነገረ መለኮት ሰውና የቅድመ ግንዛቤያዊነት (presuppositionalism) አመለካከት አራማጅ ነው።

ሶቅራጥስ (Socrates):- ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ470-399 የኖረ እጅግ በጣም ታዋቂ የሆነ የጥንቷ የግሪክ ፈላስፋ ነው።

አርስጣጣሊስ (Aristotle):- ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ384-322 የኖረ በጣም ታዋቂ የሆነ የጥንቷ ግሪክ ፈላስፋ ነው።

አፍላጦን (Plato):- ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ427- 347 የኖረ እጅግ በጣም ታዋቂ የጥንቷ ግሪክ ፈላስፋ ነው።

ሲ.ኤስ ሉዊስ (C.S.Lewis):- ከ1898-1963 ዓ/ም የኖረ እንግሊዛዊ ስመ ጥር የሥነ ጽሑፍ ሊቅና የክርስትና እምነት አቃቤ እምነት ነው።

ሬን ዲካርት (Rene Descartes):- ከ1596-1650 ዓ/ም የኖረ ፈረንሳዊ ፈላስፋና የዘመናዊው ፍልስፍና አባት ነው።

# መፍትሔ ቃላት

1. ኑባሬ (being) - ሥርወ ቃሉ "ነቢር" ሲሆን አኗኗር፡ ኑሮ፣ አቀማመጥ መኖር ማለት ነው::

2. ንጽረተ ዓለም (World View)- ሥርወ ቃሉ "ነጽሮ" ሲሆን የዓለም አመለካከት፣ ዕይታ፣ አስተያየት ማለት ነው:: ሰዎች ስለሚያካብባቸው ዓለም ያላቸውን አጠቃላይ አመለካከትና ጽንሰ ሐሳብ ያሳያል::

3. ሕሊናዊ ( Subjective)- ሥርወ ቃሉ "ኀለየ" ሲሆን የሐሳብ ሥራ፣ ኀቡእ፣ ረቂቅ፣ ውስጣዊ፣ ድብቅ፣ካሳቢው በቀር በሌላ የማይታወቅ ሲሆን በሰው ንቃተ ሕሊና ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ ያመለክታል::

4. አመክንዮ ( Reason) - "አመክንዮ" ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ምክንያት ሰጠ ወይም አቀረበ ማለት ነው::

5. እምነታዊነት ( Fideism)- ከክርስትናዊ የዐቃቤ እምነት አኳያ ያለ አመክንዮ ወይም ማስረጃ፣ በማመን ብቻ ዕውቀት ማግኘት የሚል አስተምሮ ነው::

6. ነገረ መለኮት (Theology) -ትምህርተ እግዚአብሔር ነው::



7. ተሠግዎ (Incarnation) -ሥጋ መኾን፣ሥጋ መልበስ ማለት ሲሆን የክርስቶስን ሥጋ መኾን ያሳያል::

8. ድነት (Salvation) - በወንጌል አማካይነት ንስሐ በመግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን፣ በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደት በማግኘት የዘላለም "ሕይወት" ማግኘት ነው::

9 ተምህሮነት (Scholasticism)- "ተምህሮ" ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን በቃልና በጽሑፍ ማጥናት ማለት ነው፤ ተምህሮነት (Scholasticism)- ተምህሮ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን በቃልና በጽሑፍ ማጥናት ማለት ነው፤ ተምህሮነት የአፍላጦንንና የአርስጣጣሊስን ፍልስፍናዎች ከነገረ መለኮት ጋር በማዋሃድ ለእምነት ምክኑያዊ መሠረት መስጠት ነው::

10. ተሐድሶ (Reformation)- በ16ኛው ክፍለ ዘመን ማርቲን ሉተር መጽሐፍ ቅዱስ የእምነታችንና የምግባራችን ብቸኛ መመሪያ ነው፤ ጽድቅም በእምነት ብቻ ነው ብሎ ከካቶሊክ ቤ/ክን በመውጣቱ የተካሄደው የተሃድሶ እንቅስቃሴ ነው::

11. ኢጣሬ/እጥርጥር (Summary)- በምጥን ወይም በአጭር ዐረፍተ ነገር ዋና ዋና ነጥቦችን ማስፈር ነው፤

12. <u>ሕልውናነት</u> (Existentialism)- ከምንነት(Essence) ህልዎት (existence) ይቀድማል በማለት ለአንድ ነገር በጣም አስፈላጊው ነገር መኖሩ እንጂ ምንነቱ አይደለም የሚል ፍልስፍና ነው::

13. <u>ልዩ መገለጥ</u> ( Special Revelation)-እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ መልበስ በሰዎች መካከል ራሱን የገለጠበት መገለጥ ነው::

14. <u>አጠቃላይ መገለጥ</u> (General Revelation)- እግዚአብሔር በተፈጥሮ፣ በሰው ሕሊናና በታሪክ አማካይነት ለሰው ልጆች ሁሉ በየትኛውም ሥፍራና በማንኛውም ጊዜ የገለጠበትና እየገለጠበትም ያለ መገለጥ ነው::

15. <u>ለዘብተኝነት</u> ( Liberalism)- ከድኅረ አብርሆት በኋላ ትውፊታዊው አስተምህሮና ልምምድ አዲስ ትርጉም ወይም ለውጥ ያስፈልገዋል ብሎ የተነሳ እንቅስቃሴ ነው::

16. <u>አምላከኛውያን</u> (Deists) -እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ እርሱ ጣልቃ ሳይገባ ልክ እንደ ሰዓት በፈጠረላት የተፈጥሮ ሕግ በራሷ እንድትሰራ ተዋት የሚል ፍልስፍና ነው::



17. <u>ሀቃቤ እምነት</u> (Apologetics) የነገረ መለኮት ወይም የፍልስፍና ዘርፍ ሆኖ "ከተለያዩ አስተምህሮዎችና ልምምዶች አኳያ ለክርስትና እምነት ጤናማነት የሚጋደል ዘርፍ ነው::"

18. <u>እውነታ</u> (Reality)-እውን የመሆን ወይም የሐልዎት ልቀት (Quality) ነው::

19. <u>ትምህርተ ውድቀት</u> (Doctrine of Fall) አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሳቸው ምክንያት ኃጢአትና ሞት በሰው ላይ እንደሰለጠነና ከእግዚአብሔር እንደተለዩ የሚያስተምር አስተምህሮ ነው::

20. <u>ኢ-አመክንዮአዊ</u> (Irrational) -ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም በቂ ምክንያት ያልቀረበበት ማለት ነው::

# End notes:

[1]Frederic Brahami, Le Scepticism de Montaigne (Paris: Presses Univerisitaires de France, 1997) P. 29 as quoted in Ann Hartle, 'The Dialectic of Faith and Reason in The Essays of Montaigne'= Faith and Philosopy 3 ( July 2001): 324.

እምነታዊነት (Fideism) ዕውቀትን ወደ እምነት የሚለውጥ ወይም ደግሞ ከዕውቀት ይልቅ ለእምነት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ማንኛውም አስተምህሮ እምነታዊ ይባላል:: ይህ ጽንሰ ሐሳብ በአጠቃላይ የሐሳባዊ ፍልስፍናን . ባሕርይ የሚገልጽ ነው:: ሐሳባዊነት ለሂደት ዕውቀት መንፈሳዊ ባሕርይና ለተ ደራጊው ዲበተፈጥሮአዊ ህልውና ስለሚሰጥ ደረስኩበት የሚለው ዕውቀት ተጨባጭነት የሌለው በእምነት ላይ የተመሠረተ ነው:: በዚህ ፍልስፍና ውስጥ ለሐሳብ የበላይነትና ለመንፈሳዊ ምክንያቶች የሚሰጠው ሚና በእምነት የተደገፈ እንጂ ከተረጋገጠ ዕውቀት የመነጨ አይደለም:: ዲበተፈጥሮአዊ የሆነ ነገር ሁሉ ለሕዋሳት የማይገለጥ ወይም ደግሞ በተ ግባር ሊረጋገጥ የማይችል በመሆኑ እምነታዊነት የሰውን የዕውቀት ችሎታ የሚበክል ነው (የማርክሲ



ዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978፣ ገጽ 334)::

[2] የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፤ (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤አዲስ አበባ1978፤)፤ ገጽ 273::

[3] C. Stephen Evans, Pocket Dictionary of Apologetics and Philosophy of Religion (IL: Intervarsity Press, 2002), P. 99.

[4] Norman L. Geisler and Paul Feinberg, Introduction to Philosophy (MI: Baker Books House, 1980), P. 255.

[5] Dewey J. Hoitenga, Jr., Faith And Reason From Plato To Plantinga (NY: State University of New York Press, 1991), p. 81.

[6] አማርኛመዝገበ ቃላት (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ አዲስ አበባ ዩኒ. 1993)፣ ገጽ 305::

[7] C. Stephen Evans, Pocket Dictionary of Apologetics and Philosophy of Religion (IL: InterVarsity Press, 2002), P. 44

[8] _______ Philosopy of Religion (England: InterVarsity Press, 1982), P. 178.

[9] Ibid., P. 178.

[10] Ibid., P. 178.

[11] ምህረቱ ጴ.ጉታ፤ መልስ ይኖረው ይሆን?፣ (አዲስ

አበባ፤ ኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት 1997)፤ ገጽ 102::

[12] ሥነ-አመክንዮ በሥርዐት የማሰብ ጥበብ ሲሆን የራሱ የሆኑ መርሖች ደግሞ አሉት:: ሥነ-አመክንዮ ሰዎች የሚያመነጩአቸው ሃሳቦች ከተፋለሰ የክርክር ወይም የሃሳብ መግለጫ ችግር ነፃ የሚሆኑበትን ደንቦች የሚያስተምር ዘርፍ ነው:: የግሪኩ ፈላስፋ አርስጣጣሊስ ሥርዓትን የዘረጋ ሰው ነው:: የዚህ ፈላስፋ የሥነ-አመክንዮ ስልት ምንጨታዊ ሲሆን አካሄዱም ከመንስኤ ሃሳቦች ማጠቃለያ ማውጣት ነው:: ለምሳሌ ሁለት ሃሳቦች ቢኖሩን የምንጨታዊ ሕጎችን ተከትለን አንድ መደምደሚያ ላይ ልንደርስ እንችላለን:: መንስኤ ሃሳብ 1:- ሰው ሟች ነው

መንስኤ ሃሳብ 2:- ግርማ ሰው ነው

ስለዚህ ግርማ ሟች ነው::

በተቃራኒ መልኩ ደግሞ :- ሰው ሟች ነው፣

ግርማ ሟች ነው

ስለዚህ ግርማ ሰው ነው::

ይህ መደምደሚያ የተፋለሰ ነው ምክንያቱም ግርማ ሟች ስለሆነ አይደለም ሰው የሆነው::

በሌላ መልኩ ደግሞ ሟች ነገር ሰው ብቻ አይደለም:: ሌላም ነገር ሟች ሊሆን ይችላል:: ወፎች፣ ከብት ወዘተ:: ዋና ነጥቡ መንስኤ ሃሳቦችን በመገንባት ድምዳሜ ላይ መድረስ መልክ ባለው መንገድ የተጀመረው የሥነ አመክንዮ ጥበብ በዘረጋው በአርስጣጣሊስ ነው::



[13] ምህረቱ ጴ.ጉታ፤ ክርስቲያን የሆንኩት ለምንድር ነው? (አዲስ አበባ፤ ቃለ ሕይወት መጽሔት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ቁጥር 22፤ 1993)፤ ገጽ 16::

[14] J. P. Moreland, Love Your God With All Your Mind (Colorado: NAVPRESS, 1997), P. 26.

[15] Blaise Pascal, Pensees (NY: Washington Square Press, 1965), P. 80.

[16] ምህረቱ ጴ.ጉታ፤ መልስ ይኖረው ይሆን?፣ (አዲስ አበባ፤ ኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት 1997)፤ ገጽ 98::

[17] R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 21 as quoted in, ምህረቱ ጴ.ጉታ፤ መልስ ይኖረው ይሆን?፣ (አዲስ አበባ፤ ኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት 1997)፤ ገጽ 106::

[18] Dewey J. Hoitenga, Jr., Faith And Reason From Plato To Plantinga (NY: State University of New York Press, 1991), p. 57.

[19] William L. Craig, Reasonable Faith ( IL: Crossway Books, 1994), P. 18.

[20] Auguistine, Vernon J. Bourke(ed), The Essential (USA: A Mentor- Omega Books, 1964), P. 19.

[21] Ibid., P. 19.

[22] William L. Craig, Reasonable Faith ( IL: Crossway Books, 1994), P. 17.

[23] Auguistine, Vernon J. Bourke(ed), The Essential (USA: A Mentor- Omega Books, 1964), P. 19.

(USA: A Mentor- Omega Books, 1964), P. 19.

[24] Ibid. P. 22.

[25] Ibid. P. 22.

[26] Augustine, Letters, 201.1 as quoted in Norman L. Giesler, Baker Encyclopedia of Christian Apologetics MI: Baker Books, 1999), P. 61.

[27] ST. Augustine, City Of God translated by Gerald G. Walsh, S.J., Demetruis B.Zema, S.J. and others ( USA: Image Books, 1950), P. 526.

[28] Norman L. Giesler, Baker Encyclopedia of Christian Apologetics (MI: Baker Books, 1999), P. 61.

[29] Ibid., P. 239.

[30] Ibid., P. 241.

[31] Ibid., P. 241.

[32] ST. Thomas Aquinas, On the Truth of the Catholic Faith- Summa Contra Gentiles, translated by Anton C. Pegis ( NY: Image Books, 1995), P. 74.

[33] William L. Craig, Reasonable Faith (IL: Crossway Books, 1994), P. 21.

[34] ST. Thomas Aquinas, On the Truth of the Catholic Faith- Summa Contra Gentiles, translated by Anton C. Pegis ( NY: Image Books, 1995), P. 66.

[35] Ibid., PP. 66-68.



[36] Norman L. Giesler, Baker Encyclopedia of Christian Apologetics (MI: Baker Books, 1999), P. 239.

[37] Thomas, On Truth, 14.A1.2, as quoted in Norman L. Giesler Baker Encyclopedia of Christian Apologetics (MI: Baker Books, 1999), P. 239.

[38] Thomas, Summa Theologica, 1a.2.2 as quoted in, Norman L. Giesler Baker Encyclopedia of Christian Apologetics (MI: Baker Books, 1999), P. 239.

[39] BA .Gerrish, Grace and Reason, A Study in the Theology of Luther (Oxford: Clarendo, 1962), (W.A. 275.17; 344.23; 362.15, 22; 365.18) as quoted in R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, (Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 196.

[40] Ibid. as quoted, in R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 196.

ተምህሮነት (Scholasticism) ተምህሮ ማለት፣ በጽሑፍ ማጥናት መቀጸል ማለት ሲሆን ተምህሮነትም ከዚህ የወጣ ነው:: ተምህሮነት በመካከለኛው ዘመን ለሃይማኖታዊ ንጽረተ ዓለም ንድፈሐሳባዊ መሠረት ለመስጠት ይጥር ለነበረው ሐሳባዊ ፍልስፍና የተሰጠ ስያሜ ነው:: ዋንኛ ዓላማውም የአፍላጦንንና የአርስጣጣሊስን ፍልስፍናዎች ከሥነ መለኮት ጋር በማጣጣምና በማዋሃድ ለሃይማኖት ምክኑያዊ መሠረት መስጠት

ነው። ሆኖም የሁለንታዊን ምንነት አስመልክቶ በአፍላጦንና በአርስጣጣሊስ መካከል የነበረው አለመግባባት በተምህሮትም ውስጥ በመንፀባረቁ መከፋፈልን አስከትሏል። ተምህሮነት በሦስት ዘመኖች የተከፈለ ሲሆን ከ9ኛው እስከ 13ኛው ምዕተ ዓመት የነበረው ተምህሮነት የመጀመሪያው ነበር፣ ይህም ዘመን በአዲሱ አፍላጦናዊነት የበላይነት ይመራ ነበር። ከ14ኛው እስከ 15ኛው ምዕተ ዓመት ደግሞ የብሉይ ዘመን ሲሆን ይህም ዘመን በአርስጣጣሊሳውያን ክርስቲያኖች ይመራ ነበር። ይህንንም ፍልስፍና የቀመረው ቶማስ አኩዊናስ ነበር። ከ15ኛው እስከ 16ኛው ምዕተ ዓመት የነበረው ዘመን ኋላ መጥ ተምህሮነት ሲሆን በዚህም ወቅት ዋና ጉዳይ የነበረው በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ሥነ መለኮታውያን ይካሄድ የነበረው ክርክር ነው። በ19ኛው ምዕተ ዓመት የነበረው አዲስ ተምህሮነት ሲሆን የካቶሊክ ፍልስፍናን የተለያዩ አመለካከቶች (ቶሚዝምን፣ አውገስጢኖሳዊነትን፣ ፍራንሲስካዊነትን ወዘተ...) ለማዋሃድ ጥረት የተደረገበት ነው። ፍልስፍናን ተጨባጭነት ከሌለው ከሥነ መለኮት ጋር ለማጣጣም የተደረገው ጥረት አውጥንጥኖትን፣ ጭቅጭቅን ወዘተ... ከማስከተሉ በቀር ሌላ ውጤት ሊያስገኝ ባለመቻሉ ተምህሮነት እያደር የቃላት ስንጠቃ ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ ኢተግባራዊ ዕውቀት የሚል ትርጉም እየያዘ መጥቷል። የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፤ (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ1978፤) ገጽ 222-223።

[41] Ibid. as quoted in, R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley. Classical Apologetics (MI: Academie Books. 1984). P. 196.



[42] R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 196.

[43] William L. Craig, Reasonable Faith (IL: Crossway Books, 1994), P. 36.

[44] Edward Dowey, The Kowlegde of God in Calvin's Theology (New York : Colombia University Press, 1952), 50-51 as quoted in, R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 199.

[45] John Calvin, by Joseph Pitt Wiles, David Otis Fuller (ed) Instructions in Christianity (Michigan: W.M.B. EERDMNS PUBLISHING COM, 1947), P. 30.

[46] Ibid., P. 37.

[47] Ibid., P. 38.

[48] Calvin Institutes 1.8.13 as quoted in R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 204.

[49] John Calvin, by Joseph Pitt Wiles, David Otis Fuller (ed) Instructions in Christianity (Michigan: W.M.B. EERDMNS PUBLISHING COM, 1947), P. 185.

[50] Ibid., P. 184.

[51] Ibid., P. 185.

[52] Ibid., P. 183.

[53] Ibid., P. 107.

[54] Ibid., P. 46.

[55] Ibid., P. 41.

[56] Calvin Institutes 1.8.13 as quoted in R.C. Sproul . John Gerstner . Arthur Lindsley, Classical Apologetics (MI: Academie Books, 1984), P. 205.

[57] John Calvin, by Joseph Pitt Wiles, David Otis Fuller (ed) Instructions in Christianity (Michigan: W.M.B. EERDMNS PUBLISHING COM, 1947), P. 41.

[58] Blaise Pascal, Pensees 450 (NY: Washington Square Press, 1965), P. 133.

[59] Ibid., 527, P. 151.

[60] Ibid., P. XIV.

[61] Ibid., 248, P. 79.

[62] Ibid., 277, P. 85.

[63] Ibid., 146, Pp. 49-50.

[64] Douglas Groothuis, On Pascal (Canada: Thomson Wadsworth, 2003), P. 66 (188/267).

[65] Blaise Pascal, Pensees 450 (NY: Washington Square Press, 1965), P. 84 (273).

[66] Ibid., P. 85 (278).

[67] Douglas Groothuis, On Pascal (Canada: Thomson



Wadsworth, 2003), P. 64.

[68] Ibid., P. 94.

[69] Pensees as quoted in Douglas Groothuis, On Pascal (Canada: Thomson Wadsworth, 2003), P.94 (167/269).

[70] William A. Dembski, Intelligent Design (Illinois: InterVarsity Press, 1999), P. 49.

[71] Norman L. Geisler and Paul D. Feinberg, Introduction to Philosophy (Michigan: Baker Book House, 1980), Pp. 256-268.

**ሕልውናነት (Existentialism)** በ20ኛው ምዕተ ዓመት በተለይ በአውሮፓ የተስፋፋ ሐሳባዊ ፍልስፍና ነው:: የሰው ሕልውና ከተፈጥሮአዊ ክስተቶች ውጭ የሆነ የራሱ የተለየ እውነታ ያለውና በዚህም የተነሳ ልዩ ግንዛቤ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ለማሳመን የሚጥር ፍልስፍና ነው::

.... በሕልውናነት አባባል በቁስ አካላዊም ሆነ በሐሳባዊ ፍልስፍና የሰው ልጅ ኑሮ ምንነት የሚወሰነው ከሱ ውጭ በሆኑ ምክንያቶች ነው:: ሕልውናን እንደማንኛውም ተፈጥሮአዊ ክስተት በመቁጠር ከሱ ውጭ በሆነ እውነታ የሚገዛና የሚገለጽ መሆኑ በሁለቱ ተቀናቃኝ ፍልስፍናዎች ታምኖበታል:: ለሐሳባዊ ፍልስፍና ወሳኙ ኃይል ሐሳብ ሲሆን ለቁስ አካልነትም ቁስ አካል መሆኑ ይታወቃል:: እነዚህ አመለካከቶች በምክንያቱ ላይ ቢለያዩም ሕልውናን ውጤትና መድረሻ እንጂ መነሻ አድርገው አለመቀበላቸው ገሃድ ነው:: ሕልውናን ሕይወት

በሌለው ምክንያት በመወሰናቸው ስለ ሰው ምንነት ከተሳሳተ አመለካከት ላይ እንዲደርሱ ተገደዋል::

እንደ ሕልውናነት አባባል የሰውን ሕይወት ከተፈጥሮ የሚለየው ዋናው ቁም ነገር በግዴታ ሕግ ያለመገዛቱ ጉዳይ ነው:: ማንኛውም ክስተት በግዴታ የሚገዛ ሲሆን ሰውን ግን የንቃተ ሕሊ ናው መኖር ከግዴታ ግዛት ውጭ ስለሚያደርገው የሰው ሕልውና የሚገለጸው በምርጫ ችሎታ ሆኖ እናገኘዋለን:: አንድን ነገር ጥሩ ወይም መጥፎ፣ እውነት ወይም ሃሰት የሚያደርገው ሕልውና ነው:: ለግዴታ ጥሩ ወይም መጥፎ የሆነ ነገር የለም:: እነዚህን ፍቺዎች ለመስ ጠት የሚችለው የምርጫ ችሎታ ወይም ሕልውናዊ ምክንያት ብቻ ነው:: በመሆኑም ሕልውና ከሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ሊገ ለጽ አይችልም:: ሕልውናነት እራሱን የቻለ ራሱን በራሱ ብቻ ሊያስረዳ የሚችል እውነታ ነው::

ወይም ሕልውናዊ ምክንያት ብቻ ነው:: በመሆኑም ሕልውና ከሱ ውጭ በሆነ ምክንያት ሊገለጽ አይችልም:: ሕልውናነት እራሱን የቻለ ራሱን በራሱ ብቻ ሊያስረዳ የሚችል እውነታ ነው::

ሕልውናነት ሁለት አመለካከቶችን አጣምሮ የያዘ ነው፤ እነሱም ሃይማኖታዊ ሕልውናነትና ኢእምነታዊ ሕልውናነት ናቸው:: የመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሙሉ ነፃነት ሰጥቶታል የሚል ሲሆን ሁለተኛው እግዚአብሔር ባለመኖሩ ሰው ለሚሰራው ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂ ነው ይላል::



/የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ:- ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት 1978 ገጽ 10-11/

ለዘብተኝነት በአሥራ ዘጠነኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፕሮቴስታንቶች ነገረ መለኮተ ዙሪያ ተነስቶ የነበረ እንቅስቃሴ ነው:: የለዘብተኛነት ቁልፍ ግብ የክርስትናን እምነት ከሳይንስ ጋር ማስታረቅ ነው:: ከዚህም የተነሳ ለዘብተኝነት የእግዚአብሔርን ቃል ባለሥልጣንነት አይቀበልም:: በተአምራት አያምንም:: ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑ ቀርቶ ታላቅ የሥነ-ምግባር አስተማሪ ነው::

[72] Norman L. Giesler, Baker Encyclopedia of Christian Apologetics (MI: Baker Books, 1999), P. 239.

[73] Michael Peterson, William Hasker, Bruce Reichenbach, David Basinger, Reason and Religious Belief (3rd ed.), (New York: Oxford University Press, 2003), P. 45.

[74] C. Stephen Evans, Philosopy of Religion (England: InterVarsity Press, 1982), P. 17.

[75] Ibid. P. 17.

[76] Peter Kreeft and Ronald Tacelli Hand Book of Christian Apologetics (Illinois: InterVarsity Press, 1994), P. 15.

[77] Ibid., P. 43.

[78] Ibid., P. 43.

[79] Ibid., P. 79.

[80] Pensees, as quoted in Peter Kreeft and Ronald Tacelli, Hand Book of Christian Apologetics (Illinois: InterVarsity Press, 1994), P. 36.

[81] William L. Craig, Reasonable Faith (IL: Crossway Books, 1994), P. 36.

[82] Peter Kreeft and Ronald Tacelli, Hand Book of Christian Apologetics (Illinois: InterVarsity Press, 1994), P. 29.

[83] J. I Packer , Faith: Evangelical Dictionary Of Theology: Walter A. Elwell( ed) ( Michigan: Baker Book House, 1984), P. 400.

[84] Ibid., P. 402.

[85] Dewey J. Hoitenga, Jr., Faith And Reason From Plato To Plantinga (NY: State University of New York Press, 1991), p. 38.

[86] J. I Packer , Faith: Evangelical Dictionary Of Theology: Walter A. Elwell( ed) ( Michigan: Baker Book House, 1984), P. 400.

[87] Ibid., P. 400.

[88] Ibid., P. 402.



[89] Ibid., Pp. 400- 402.

[90] Gordon Lewis, Journal of Theological Society (June 2003).

[91] Alvin Plantinga and Nicholas Wolterstroff (eds), Faith and Rationality (Notre Dame: University of Notre Dame Press, 1983), P. 15.

[92] Douglas Groothuis, On Jesus (Canada: Thomson Wadsworth, 2003), Pp. 1-95.

[93] Norman L. Geisler and Roland M. Brooks, Come Let Us Reason: An Introduction to Logical Thinking (MI: Baker Books House, 1990), P. 7.

[94] Ibid., P. 7.

[95] Ibid., P. 7.

[96] J. P. Moreland, Love Your God With All Your Mind (Colorado: NAVPRESS, 1997), Pp. 58-59.

[97] Ibid., Pp. 58-59.

[98] **ምህረቱ ጴ.ጉታ፤ መልስ ይኖረው ይሆን?፣ (አዲስ አበባ፤ ኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት 1997)፤ ገጽ 103-106::**

[99] C.S Lewis, Mere Christianity ( NY: Collier Books, Macmillan, 1943), P. 109.

[100] Daniel Taylor, The Myth of Certainty (IL: IVP, 1986), P. 70.

[101] William L. Craig, Reasonable Faith (IL: Crossway Books, 1994), P. 34.



## Bibliography


*አማርኛ መዝገበ ቃላት (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል*፤ **አዲስ አበባ ዩኒ. 1993**

Aquinas, ST. Thomas. *On the Truth of the Catholic Faith- Summa Contra Gentiles*, translated by Anton C. Pegis (NY: Image Books, 1995.

Augustine, Vernon J. Bourke(ed), *The Essential .*USA: A Mentor- Omega Books, 1964.

________. *City Of God* translated by Gerald G. Walsh, S.J., Demetruis B.Zema, S.J. and others USA: Image Books, 1950

Barth, Karl. *Church Dogmatics*. Vol. 1 G.T. Thomson (trans.) Edinburgh: T. and T. Clark, 1936.

Calvin, John, by Joseph Pitt Wiles, David Otis Fuller (ed).*Instructions in Christianity.* Michigan: W.M.B. EERDMNS PUBLISHING COM, 1947.

_______. *Institutes of The Christian Religion*. Henry Beveridge (trans.) V.1. MI: WM B. EERD MANS Pub., 1953.

Craig. L. William. *Reasonable Faith.* IL: Crossway Books, 1994.

Dembesky, William. *Intelligent Design.* IL: Intervarsity Press. 1999.

Evans, C. Stephen. *Philosophy of Religion*. England: Inter varsity Press, 1982.

________. *Pocket Dictionary of Apologetics and Philosophy of Religion IL: Intervarsity Press, 2002.*

Enock, Stumpf Samuel. *Socrates To Satre. A History of Phi losophy*. London: Mcgraw- Hill Book, 1996.

*Faith and Philosopy* 3 (July 2001): 324.

Geisler, L.Norman and Brooks, M. Roland. *Come Let Us Reason: An Introduction to Logical Thinking*. MI: Baker Books House, 1990.

________.and Feinberg, Paul. *Introduction to Philosophy.* I: Baker Books House, 1980.

________.*Baker Encyclopedia of Christian Apologetics.* MI: Baker Books, 1999.

Groothuis, Douglas. *On Jesus* .Canada: Thomson Wadsworth, 2003.

________.*On Pascal* .Canada: Thomson Wadsworth, 2003.

ጉታ ጴ. ምህረቱ፤ *መልስ ይኖረው ይሆን?*አዲስ አበባ፤ ኤስ አይ ኤም ማተሚያ ቤት 1997

Guta, P. Mihretu. *Jesus In The Gospels*. Koinonia Newspa per. March 2005, 11th ed. Addis Ababa: Interna tional Evangelical Church.

Ganssle E. Gregory. *Thinking About God: First Steps in Phi losophy*. IL: IVP, 2004.



Hoitenga, J (Jr), Dewey. *Faith and Reason from Plato to Plantinga* .NY: State University of New York Press, 1991.

Kreeft, Peter and Tacelli, Ronald. *Hand Book of Christian Apologetics.* IL: Intervarsity Press, 1994.

Lewis, C.S. *Mere Christianity* .NY: Collier Books, Macmil lan, 1943.

Lewis, Gordon. *Journal of Theological Society* (June 2003).

Moreland, J. P. *Love Your God With All Your Mind* .Colorado: NavPress, 1997.

_____ and Craig Lane William. *Philosophical Foundations for Christian Worldview*. IL: IVP, 2003.

McGrath, E. Alister. *Christian Theology.* 2nd ed. UK: Black well Publishers, 1994.

Pascal, Blaise. *Pensees*. NY: Washington Square Press, 1965.

Peterson, Michael, Hasker, William, Reichenbach Bruce and others. *Reason and Religious Belief* 3rd ed. New York: Oxford University Press, 2003.

Plantinga, Alvin and Wolterstroff, Nicholas (eds). *Faith and Rationality.* Notre Dame: University of Noter Dame Press, 1983.

Patrick, Hurley. *A Concise Introduction To Logic*. 5th ed. Wadsworth Pub, California, 1994.

Rene, Descartes. *Meditations On First Philosophy*. Laurence J. Lafleur ( trans.). Indianapolis¨Bobbs- Merril Edu cational Pub., 1951.

Stumpf, Samuel Enoch. *Socrates to Sartre:A History of Philosophy.* Toronto: Mc Graw Hill Book Camo; 1966

Sproul R.C. Gerstner, John and Lindsley, Arthur. *Classical Apologetics* .MI: Academia Books, 1984.

Sire, W. James. *Habits of The Mind: Intellectual Life as a Christian Calling*. IL: IVP, 2000.

Taylor, Daniel. *The Myth of Certainty.*IL: IVP, 1986.

*የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት*፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤አዲስ አበባ1978



# INDEX—ንዑሳን አርዕስቶች

## ፀሐፍት (Authors)

1. አውግስጢኖስ (Augustine) 14,(23-28) 30,36,51,53,58,59,64,93,96
2. አርስጣጣሊሳዊ (Aristotleian) አርስጣጣሊስ (Aristotle)25,28,36, 29,33-36,51,53,58,64,93,96
3. አኪውነስ፣ቶማስ( Aquinas, Thomas) 28-33,36, 51,53,58,64,93,96
4. ባርት፣ ካርል (Barth,Karl) 55,60,93,97
5. ቡልትማን፣ሩዶልፍ (Bultmann, Rudolf) 55,59,60,93,97
6. ካልቪን፣ ጆን (Calvin,John)- 39-45,52,53,93,96
7. ዘ እስክንድርያ (Clement of Alexandria)- 57,60,64,97
8. ክሬግ፣ዊሊያም (Craig, William) 25,38,70,94
9. ዴካርት፣ሬን (Decartes, Rene) 26,98
10. ኢቫንስ፣ ስተፈን- (Evans, Stephen) 15,16,65
11. ጌርሽ,ቢ.ኤ. (Gerrish, B.A)-37
12. ግሩታየስ፣ዳግላስ ( Groothuis, Douglas) 79

13. ጋይዝለር፣ ኖርማን፣(Giesler, Norman) 19,28,64

14. ሆትንጋ፣ ዴዊ (Hoitenga, Dewey J.)7

15. ሃርሌ፣ፓትሪክ ጄ.(Hurley, Patrick J.)

16. ዮስጦስ ሰማዕት (Justin Martyr) 57,60,64,97

17. ካንት፣ኢማኑኤል (Kant,Emmanuel) 56,57,60,93,97

18.ኪርከጋርድ፣ሶረን( Kierkegaard, Soren) 55,59,60,93,97

19. ክሬፍት፣ ፒተር (Kreeft, Peter )66

20. ፒተር፣ ክሬፍት (Petere, Kreeft) 69

21. አፍላጦን፣ (Plato) 36,98

22. ሉዊስ፣ ሲ.ኤስ (Lewis, C.S) 94,98

23. ሉተር ማርቲን (Luther, Martin) 33-38,52,53,93,96

24. ሞርላንድ፣ጄ.ፒ. (Moreland, J.P) 19,81,85

25. ፓኬር፣ ጄ.አይ (Packer, J. I.) 73,75

26 ፓስካል፣ ብሌዝ(Pascal, Blaise)- 19,20
45-51,53,59,69,93,96

27. ሶቅራጥስ (Socrates) 98,99,91

28. እስፕሮል፣አር.ሲ.(Sproul,R.C) 20,21

29.ስፒኖዛ፣ቤንዲክት(Spinoza,Bendict)-54
56,57,60,93,96

30. ሽየርማከር፣ፍሬድሪክ (Schleiermacher, Friedrich)54,97



31. ታስሊ ሮናልድ (Tacelli, Ronald) 66,69

32. ጠርጡሊያኖስ ( Turtullian)-58 ,61,64,97

33. ቴይለር፣ዳንኤል ( Taylor,Daniel) 94

34. ቫንቲል፣ ኮርነሊየስ (Van Til Cornelius) -50,61,97

## ንዑሳን አርዕስቶች (Subject)

1. Apologetics- 71, 102, Apologist-19
2. Arguments- 69,94
3. Beings-31,99
4. Belief -25
5. Concept-24
6. Deductive-25
7. Deists-57,101
8. Doctrine of fall- 81,102
9. The doctrine of the Knowledge of God-39
10. Evidence-47
11. Existentialism- 55,101
12. Faculty -15
13. Faith -16,19
14. Fideism- 12, 25,48,65,93,99
15. General Revelation- 101,62
16. Heart dimension-21
17. Incarnation- 30,100
18. Irrational- 94,102
19. Knowing Order-61
20.Knowledge -25
21.Knowledge dimension-21



21. (Logic)- 18
22.Medieval- 64
23. Natural reason-32
24.Ontological Order- 61,62
25.Rationalism-65,93
26Reality-67,102
27.Reason (አመክንዮ) -14,17,99
28.Reformation- 100
29.Revelation -55,57
30.Salvation-33,36,100
31.Scholasticism- 35,100
32.Seeing -25
33. Secular-16
34. Submit-50
35. Subtuagint-24
36.Summary-38,100
37.Special Revelation- 101
38..Subjective -16,99
39.The Law of Identity-18
40.The Law of non- Contradiction 18
41.Tool-48

42. Trust dimension- 22

43. Theology-37,99

44. Trust-16

45. Vision- 25

46. Worldview -15,99